# <u>የምዕራቡ ዓለም ከኢትዮጵያ ምንድነው የሚፈልገው ?</u>
# <u>እኛስ በምዕራቡ ዓለም ላይ ያለን አመለካከት ምን ይመስላል?</u>

**<u>ለመንደርደሪያ ያህል !!</u>**

ከዛሬ ሰላሳ ዐመት በፊት የተማሪው እንቅስቃሴ ከረጅም ጌዜ ውጣ ውረድ ትግል በኋላ የደረሰበት መደምደሚያ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠላቶች ፊዩዳሊዝም ፣ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ናቸው የሚል ነበር። በጊዜው የተማሪው እንቅስቃሴ እነዚህን ሶስት ኃይሎች እንደ ዋና ጠላት ያየው ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መከበር ፣ ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለብሄራዊ ነፃነት እንቅፋት ናቸው ብሎ በማመኑ ነበር። ስለዚህም እነዚህ ጠላቶች እስካልተወገዱ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝቦች በምንም ዐይነት ዕውነተኛ ነፃነትን ለመጎናፀፍ አን ደማይችሉ ደመደመ። ይህ ዐይነቱ ግምገማ ከሜታፊዚክስ አንፃር የተሟላ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ባይቻልም በአጠቃላይ ሲታይ በጊዜው የተማሪው እንቅስቃሴ ትግል አንድ መመሪያ እንደነበረው መረዳት ይቻላል። ዝም ብሎ በጭፍኑ የሚጓዝ እንቅስቃሴ እንዳልነበር የተማሪውን እንቅስቃሴ ታሪክ ላገላበጠ ወዲያውኑ በቀላሉ ሊገነዘበው ይችላል።

በጊዜው የተማሪው እንቅስቃሴ ችግር ፣ 1ኛ) ሜታፊዚክሳዊ ባህርይ አልነበረውም። ማለትም ወደ ውስጥ ጠላት የሚለውን ኃይል ከንቃተ ህሊና ብስለት ጉድለት ጋር ለማያያዝ ያለመቻሉ የማያስፈልግ ህብረተሰብአዊ ቅራኔና የእርስ በርስ ግጭት እንዲፈጠርና መዘዙም እስካሁን ድረስ እንዲዘልቅ ለማድረግ በቃ። በሌላ አነጋገር በደፈናው ፊዩዳሊዝም የኢትዮጵያ ጠላት ነው ብሎ ከመነሳት ይልቅ የህብረተሰባችንን የንቃተ ህሊና ዕድገት በመገምገም ለምንስ አንድ የህብረተሰብ ክፍል ለዕድገት እንቅፋት ሊሆን ይችላል ብሎ ጠለቅ ያለ ምርምር በማድረግ ወደ ተሻለ የትግል ስልት በመሸጋገር ህብረተሰብአዊ ቅራኔ እን ዳይፈጠር አዎንታዊ አስተዋፅኦ ማድረግ በቻለ ነበር። በተለይም የተወሰነው የተማሪ እን ቅስቃሴ ክንፍ እጅግ ችኩልነት ስላጠቃው ከጥናትና ከምርምር ይልቅ ወደ ግብግብ በማድላትና በዚህም ድልን መጎናጸፍ ይቻላል ብሎ በማመኑ እንዳየነው የአገራችንን ችግር የባሰ ውስብስብና በቀላሉ ሊፈታ እንዳይችል አድርጎ አለፈ።

2ኛ) ሌላው የተማሪው እንቅስቃሴ ችግር ኢምፔሪያሊዝም የሚለውን ፅንሰ-ሃሳብና መንግስትና የመንግስት መዋቅር በዕድገትና በፀረ-ዕድገት ላይ የሚኖራቸውን ሚናና ተፅዕኖ በደንብ የተገነዘበ አልነበረም። ከፖለቲካ ፣ ከኢኮኖሚና ከርዕዮተ-ዓለም አኳያ ሰፊ ግምገማ በማድረግ የኢምፔሪያሊዝምን ፣ በተለይም የአሜሪካን ኤምፔሪያሊዝምን የተቀነባበረ ሴራ ለመዋጋት የሚያስችለው መሳሪያ ለማዳበር በፍጹም አልቻለም። ስለሆነም የኢምፔሪያሊዝምን ልዩ ልዩ ባህርዮችና ገጽታዎች ፣ ማለትም ፖለቲካዊ ፣ርዕዮተ ዓለማዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ሚሊታሪያዊ ባህርዮችን ጠለቅ ብሎ ለማጥናት ዕድል ለማግኘት ባለመቻሉ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ለዕውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ህይወትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲሁም ለብሄራዊ ነፃነት የሚደረገውን ትግል በበቂው ማሳየት አልቻለም። በመሆኑም ጊዜ ወስዶ የኢምፔሪያሊዝምን ምንነት በበቂው ለመረዳትና በአንድነት ህዝቡን ለማታገል ያልቻለው የተማሪ እንቅስቃሴ ስልጣን ለመያዝ በሚደረገው ትግል ብቻ አትኩሮ ስላደረገ እዋጋለሁ ያለው ጠላት ሰለባ ሆነ። ሲአኤ ባጠመደው ወጥመድ ሰተት ብሎ የገባው ጥቂቱ የተማረ ኃይል በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ኮሙኒዝምን እዋጋለሁ በሚል ሽፋን ስር ፣ በመሰረቱ ግን ዲሞክራሲያዊ ለውጥን አጥብቆ የሚጠላው የውስጥ አርበኛ በአንድነት በመተባበር ኢትዮጵያችንን የደም አምባ ለማድረግ በቁ። ከዚህም በላይ ደግሞ ከሶቭየቱ የኢምፔረያሊስት ጋር የተወዳጀው ኃይል ሀቀኛው ሶሻሊዝም ይህኛው ብቻ ነው ፤ ይህንን ያልተቀበለ የአብዮቱ ጠላት ነው በሚል ሽፋን ስር ፀረ-ዕድገትና ፀረ-ዲሞክራሲ ትግሉን በማጧጧፍ በስንት ችግር አገራችን የአፈራቻቸውን ወርቅ ምሁራን እንዲቀጩ አደረገ። ይህም በራሱ ምንም የፖለቲካ ስልት በሌለው የወታደር አገዛዝ መዳፍ ስር በመውደቅ ጠቅላለውን የህብረተሰብ አረማመድና ዕድገት ማዘበራረቁን ተያያዘው። ዓለም በሁለት

የተከፈለች ነች በሚል ምንም ሳይንሳዊ መሰረት በሌለው አነጋገር የሶሻሊስቱን ካምፕ ያልመረጠ መደምስስ አለበት እያለ በተጨባጭ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ነፃነት ለማኮላሸት ፣ ምሁሮቿን ለመደምሰስ በመጣው የኬጂቢ ሃይል ወጥመድ ውስጥ በመውደቅ በበኩሉ የአገራችንን መከስከስ አፋጠነ።

ወደ ኋላ መለስ ብለን የኢትዮጵያን ህዝቦች የአብዮት ታሪክ ስንገመግም የምንደርስበት ድምደማ የቱን ያህል ፣ 1ኛ) በኢትዮጵያ የምሁር እንቅስቃሴ ውስጥ ሰፋ ያለ ጥናትና ውይይት ለማድረግ ገቱ እንደሌለ ፣ 2ኛ) የተወሰኑ መፈክሮችን ብቻ በማንጠልጠልና እነሱን የትግል መሳሪያ በማድረግ ወደፊት ሽምጫ ማድረግ ፣ 3ኛ) ግለ ሰቦችን መናቅና ስም ማጥፋት ፣ 4ኛ) የሳይንስና የቲዎሪን አስፈላጊነት በፍጹም ቁጥር ውስጥ አለማስገባትና ፣ 5ኛ) ከዚህም በመነሳት የህብረሰተብአችንን አወቃቀርና ዓለም አቀፋዊውን ሁኔታ በቅጡ በመገምገም እንዴት አድርገን ኃይላችንን በመሰብሰብ ወደ ውስጥ ያተኮረ ለዕድገትና ለዲሞክራሲ ማበብ የሚያመች የትግል ስልት መንደፍ እንችላለን ወደ ሚለው መሰረታዊ ሃሳብ ላይ አለማትኮር። እነዚህ ባህሪዎቻችን በመሆንና እስከዛሬ ድረስ አንቀውን በመያዝ ከስሜታዊ ትግል ለመላቀቅ በፍጹም አልቻልንም።

ይህ የኢትዮጵያ ምሁር ድክመት ፣ በተለይም ደግሞ ለዕድገትና ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል የቲዎሪን ጉዳይ ከብዙ አቅጣጫዎች አንስቶ መወያየትና ወደ አንዳች ስምምነት ደርሶ በሙሉ ኃይል ለአገር ግንባታ ያለመነሳት የግዴታ በውጭ ኃይሎች እንድንጠቃ አድርጎናል። በዚህ ላይ ግሞ አንዳንዶች ሆን ብለው አገራችንና ህዝባችን የስልጣኔና የዲሞክራሲ ባለቤት እንዳይሆኑ ከውጭ ኃይሎች ጋር በማበር የተቀነባበረ ሴራ በሚያደርጉት ትግል ውስጥ አን ዳንዶቻችን ሰምጠን በመግባታችን በጠላትና በወዳጅ መሀከል ያለውን ልዩነት በግልጽ ለመረዳት አልቻልንም። በተለይም ከአስራ አምስት ዓመት ጀምሮ ዓለም ወደ አንድ አቅጣጫ እያመራች ነው ፤ እኛም እዚያ ውስጥ ገብተን መወዳደር አለብን በሚለው ፈሊጥ በመጠመዳችን በግልጽም ሆነ በይፋ በተቀነባበረ መልክ የሚያጠቃንን ጠላት ፣ ብሄራዊ ነፃነታችንን ተቀናቅኖ የልመና ዘመናችንን የሚያራዝመውን የውጭ ኃይል ጠጋ ብለን ለመመርመር በፍጹም የተሳነን ይመስለል። ከዚህ በመነሳት ዛሬ የገባንበትን አዘቅት ለመመርመር በዓለም ላይ የተካሄደውን የኃይል አሰላለፍ ለውጥና በእኛ አስተሳሰብና በትግላችን ያመጣውን ተጽዕኖ ጠጋ ብለን ለመመርመር እንሞክር። በመጀመሪያ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚመራው የምዕራቡ ዓለም በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን የነበረውን ተጽዕኖ አጠር ባለ መልኩ እንመልከት።

EthioLion.com

## <u>የምዕራቡ ተፅዕኖና ሚና እንዲሁም የኢትየጵያ ዕድገት በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን</u>

ከጣሊያን መሸነፍና መባረር በኋላ ኢትዮጵያ ነፃነቷን ስትቀዳጅ እንደ አንድ የተከበረች አገር ሆና ለህዝቦቿ ሙሉ በሙሉ ነፃነትን ለማጎናፀፍ የሚያስችላት ብዙ ነገሮች ይጎሏት ነበር። በመጀመሪያ በአምስት ዓመት የወረራ ዘመን የፈራረሰው የማዕከላዊ አስተዳደር እንደገና በአዲስ መልክ መዋቀር ነበረበት። ሁለተኛ በወረራው ዘመን በገፍ የተገደለውን የምሁር ኃይል ሊተካ የሚችል አዲስ ትውልድ ማፍራት አስፈላጊ ነበር። ከዚህም በላይ ደግሞ ፣ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ እንደ አንድ ኢኮኖሚያዊ ኃይል ሊንቀሳቀስ የሚችል የከበርቴ መደብ በፍጹም አልነበረም። ቀድሞውኑ መሰረቱን በተዝረከረከ ኢኮኖሚ ላይ አድርጎ የተዋቀረው ማዕከላዊ አስተዳደር ከጣሊያን መባረር በኋላ በራሱ ሊጓዝ የሚያስችለው የዕውቀት ፣ የፖለቲካ ፣ የሚሊታሪና የኢኮኖሚ መሰረት አልነበረውም። በዚህም ምክንያት ለእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ በሩን ከፍቶ በመስጠት እነሰም በዛም ለገበያ ኢኮኖሚ ዕድገት ሊሆኑ የሚችሉ ፣ የጣሊያን ወራሪ ኃይል የአቋቋማቸውን ኢንዱስትሪዎች እየተነቀሉ ወደ ባህር ማዶ ተወሰዱ። እ.አ በ1942 ዓ.ም በእንግሊዝና በኢትዮጵያ መንግስት መሀከል የተደረገው ስምምነት የሚያረጋግጠው ኢትዮጵያ ከጣሊያን ወራሪ ብትላቀቅም ፣ በሌላ ወገን ደግሞ

ስምምነቱ እንግሊዝ በማንኛውም ኢትዮጵያ ጉዳዮች ጣልቃ እንድትገባ ሲያመቻች ፣ ሀብቷም እንዲዘረፍና የወደፊት እድገቷም ቀጭጮ እንዲቀር ሁኔታውን ያመቻቸ ነው። በዚህ ተግባሯ እንግሊዝ በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን ተቀናቃኝ እንዳይኖሯት ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ወደ ሌሎች አገሮች እንዳይስፋፋና የኢንዱስትሪ አብዮትም ባለቤት እንዳይሆኑ ትሸርብ የነበረውን ተንኮል የኢትዮጵያን መንግስት ደካማ ጎን ተጠቅማ የተተከሉትን ኢንዱስትሪዎችና የመመለለሻና የመገናኛ መስመሮች አፈራርሳ ጠርጋ ወሰደች። በዚህም ምክንያት ኢኮኖሚው እንደገና በአዲስ መልክ መደራጀት ነበረበት። ይህ ደግሞ አዲስ ከተዋቀረው ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ አወቃቀር ውጭ ሊሆን የሚችል አልነበረም። እ.አ. ከ1945 ዓ.ም በኋላ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዋቀረው ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ርዕዮተ ዓለማዊና ሚሊታሪያዊ የኃይል አሰላለፍ በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ዕድገት አረማመድ ላይ ጫናውን እንዲጥልና ጠቅላለው የህብረተሰባችን አወቃቀርም ከውስጥ ዕድገትን እንዲቀናቀንና ወደ ውጭ ደግሞ ጥገኝነትን እንዲያጠናክር ሆኖ በመዋቀር የኢትዮጵያ ህዝቦች ዕድል ተጨናግፎ እንዲቀር አድርጓል። እነዚህን ሂደቶች አንድ በአንድ ወረድ ብለን እንመልከት።

በመጀመሪያ ደረጃ በአፄ ኃይለስላሴ የሚመራው አዲሱ የገዢ መደብ አስተዳደሩን ለሱ አገዛዝ በሚመቸው መልክ ማዋቀር ነበረበት። በገጠርና በአንዳንድ አነስተኛ ከተማዎች ከፊል ፊዩዳላዊ አስተዳደር ሲዋቀር ፣ የዚህ አዲስ አስተዳደር አወቃቀር በየቦታው ከተማዎችን መቆርቆርና ሀብት እንዲዳብር የስራ ክፍፍሉን በአዲስ መልክ ማደራጀትና ህብረተሰቡን የጠቅላላው ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ማድረግ ሳይሆን የማዕከላዊ መንግስቱን የህብረተሰብ መሰረት ለማጠናከርና ሀብት ከታች ወደ ላይ እንዲሽጋሸግ በማድረግ የገዢውን መደብ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ህብረተሰብአዊ ተቋም በጠንካራ መሰረት ላይ ለማቆም ነበር። በዚህም ምክንያት በተለይም በገጠር የሚኖረው ህዝብ ከአስተዳደሩ ከመገለሉም ባሻገር በመንግስትና በህዝብ መሀከል ምንም ዐይነት ግኑኝነት እንዳይፈጠር በማድረግ የህብረተሰቡ የመፍጠር ችሎታ እንዲዳሸቅና ህዝቡ በድህነት እንዲማቅቅ ለማድረግ የበቃ ከህዝብ ፍላጎት ጋር በፍጹም ሊጓዝ የሚችል አስተዳደር እንዳይገነባ ሆነ። ስለሆነም ጠቅላላው የገጠርና የትናንሽ ከተማዎች ኗሪው ህዝብ በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ተደራጅቶ እራሱን በማን ቀሳቀስና የስራ ክፍፍሉን በማዳበር ኢትዮጵያን እንደ አንድ ህብረ-ብሄር ለመገንባት የሚያስችለውን የተፈጥሮ ኃይል እንዲነፈግ ተገደደ። ወደ ከተማዎች ስንሄድ አዲስ የተቋቋመው ቢሮክራሲ በአንድ በኩል የገዢው መደብ መሰረት በመሆን ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ከውጭ ኃይል ጋር ያለውን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ርዕዮተ ዓለማዊና ሚሊታራዊ ግኑኝነት በማጠናከር ኢትዮጵያ ራሷን ችላ በጸና የማቴሪያላዊ መሰረት ላይ እንዳትገነባና ለህዝቦቿ አለኝታ እንዳትሆን የተቀነባበረና ውስብስብ የሆነ የጭቆና ስርዓት ዘረጋ። ይህ ሁኔታ የግዴታ ለአሜሪካን ኤምፔሪያሊዝም መንገድ ጠራጊ በመሆን በተለይም በአዲሱ ትውልድና በቢሮክራሲው መደብ ላይ ከፍተኛ የህሊና ጫና ለማድረግ አስቻለው። አዲስ የተዋቀረውም የመንግሰት መኪና ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው የምዕራቡ ዓለም ሰርጎ መግቢያ መንገድ በመሆንና በስራ ክፍፍል በመሰነጣጠቅ አንድ ነፃ መንግስት ሊያካሂድ የሚችለውን ውስጣዊ ጥንካሬና የህብረተሰብ ዕድገት ለማምጣት በፍጹም ተሳነው። ለምሳሌ የጦር ሰራዊቱና የአየር ኃይል በተለይም ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ተጽዕኖ እንዲያመች ሆኖ የተዘጋጀ ነበር ማለት ይቻላል። እስራኤልም ሆነ እንግሊዝ የራሳቸው የስራ ድርሻ ቢኖራቸውም ዋናው ጫናና ርዕዮተ ዓለማዊ ተጽዕኖ የሚመጣውና ከፍተኛውን ሚና በመንግስቱ መኪና ላይ የሚጫወተው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ነበር ማለት ይቻላል። ወደ ፖሊስ ስንመጣ በተለይም የጭቆናውን መሳሪያ አቅራቢ በጊዜው እንደነ ምዕራብ ጀርመን የመሳሰሉ አገሮች እንደነበሩ የማይታበል ሀቅ ነው።

ለዚህ የምዕራቡ ኢምፔረያሊዝም ፣ በተለይም ደግሞ ለአሜሪካን ኢምፔረያሊዝም በአገራችን የህብረተሰብ ዕድገት ላይ ጫና ማድረግና የአገራችንን የዕድገት አቅጣጫ መወሰን ፣ አገዛዙ የተከተለው የተበላሸ ፖለቲካ ነፀብራቅ ነው ማለት ይቻላል። በመጀመሪያ ለአሜሪካንም ሆነ ለእንግሊዝና ለሌሎች እየተለካ የተሰጠው ለኤምባሲዎች መስሪያ የሚሆን ሰፋፊ መሬት

EthioLion.Com

የአገራችንን ህልውና በከፍተኛ ደረጃ የተቀናቀነ እንደሆነ ግልጽ ነው። በማንኛውም ታሪክና አገር ያልተደረገ እንክብካቤ ያገኘው የአሜሪካን ኢምፔሪሊዝም ኢትዮጵያ እንደ አንድ ህብረተሰብና ህብረ-ብሄር እንዳትጠነክር መሸረቢያ መንገድ አገኘ። አገራችንን ለመገነጣጠልና ለማዳከም ለሚፈልጉ ኃይሎች አመቺ ሁኔታ ተፈጠረላቸው። በዚህም ይህንን ሰፊ ጋሻ መሬትና ግቢ ተገን አድርጎ በወጣቱና በህዝባችን ላይ አማራጭ የሌለው ኃይልና ህልውናችንን ሊቆጣጠር የሚችል መሆኑን አሳመነ። ሁለተኛ በኤርትራ ውስጥ የነበረው የቃኘው ጦር ሰፈር በአካባቢው ያለውን ሁኔታ ከመቆጣጠር ባሻገር የኢትዮጵያ መካፋፈል የሚጠነሰስበት ሌላው ታሪክን ያጎደገፈ ፣ በገዢዎቻችን ሳይታሰብና አገራችንን በመናቅ ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እንደቡራኬ የተለገሰለት ነው። ይህንና ሌሎችም ጉዳዮች ተደምረው ኢትዮጵያ የምዕራቡ ዓለም ወዳጅና ኮሙኒዝምን የምትዋጋ ኃይል ተደርጋ በመወሰዱ ፣ በምዕራቡ ፖለቲካ እንድታሽና ዕድገቷም በዚሁ እንዲወሰን ተገደደ።

ይህ ነፃነትን ገፋፊ ፣ አገርን አፍራሽና ህዝብን የሚያስንቅ በመሰረቱ ግን የራስን ታሪካዊ ቦታና ምንነት ካለመረዳት የመነጨ ፖለቲካ ፣ አገዛዙ እንደ ነፃ መንግሰት እንዳይንቀሳቀስ አገደው። የመንግሰቱ ተግባርና ኃላፊነት በየጊዜው እየተጠና ህብረተሰብአዊ ችግሮችን ለመፍታትና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማምጣት እንዳይችል ሆኖ በመዋቀሩ ከፊቱ የተደቀኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ተሳነው። የመንግስቱም ተግባር በጭቆናና በጦርነት ላይ ብቻ በማትኮር የአገሪቱ ሀብት ወደ ውስጥ የስራ ክፍፍል ዳብሮ ህብረተሰብአዊ ሀብት እንዲከማችና የካፒታሊስት ኢኮኖሚ እንዳያድግ እዚያው በዚያ እንዲታሽ ሆነ። የመንግስቱ መኪናና የገዢው መደብ ታሪክን ከመስራት ይልቅ በህብረተሰቡ ላይ ዘመቻ በማድረግ የጠቅላለው ህብረተሰብ የመፍጠር ችሎታ እንዲታፈን ተደረገ። ለዚህ ደግሞ ነጭ ለባሽ የሚባለው በመሰረቱ የገዢውን መደብ ጥቅምና ደህንነት የሚጠብቅ በማሰማራት ህዝቡ በፍርሀት እንዲዋጥና በአገዛዙ ፣ በተለይም በሞናርኪው ላይ ያለው ዕምነት እንዲጠነከር በማድረግ ሰው አምላኪ ሆነ። ነፃነት የማይሰማውና በራሱ የማይተማመን ሆነ። በአፄ ኃይለስላሴ ዘመንም የታየውና "ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ" እየተባለ የሚነዛው ወሬ የንጉሳዊውን የጭቆናና የብዝበዛ አገዛዝ ርዕዮተ ዓለማዊ ድጋፍ ለመስጠት እንደነበር የማይታበል ሀቅ ነው።

በዚህ መልክ በተዋቀረ አገዛዝ ፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሆነ ሌሎች የካፒታሊስት አገሮች የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እነሱ በፈለጉት መልክ ማደራጀት እንዲችሉ አድርጎ መንገዱን አዘጋጅቶ ሰጣቸው። ለዚህ ደግሞ እ.አ ከ1945 ዓ.ም በኋላ በነፃ ገበያ ስም የዳበረው ፣ ግን ደግሞ ኋላ ቀርነትን የሚያጠነክር በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ደሀ አገሮችን እዚያው በዚያው እያሹ ለማቆየት የተተለመው አዲሱ ስትራቴጂ ሌላው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መግቢያ ቀዳዳ ነበር። ይህ አዲሱ የነፃ ገበያ ስትራቴጂ ሲቀየስ ፣ ከጦርነቱ በፊት እንደነበረው ሁኔታ የአፍርቃንና ሌሎች የላቲን አሜሪካንን አገሮች በግልጽ መበዝበዝ አይቻልም ነበር። በቀድሞው የስራ ክፍፍል ፣ ማለትም የሶስተኛውን ዓለም አገሮች ንጹህ የጥሬ ህብት አምራች አገሮች ማድረግና በዚሁ ላይ ብቻ እንዲሰለጥኑ ግልጽ የሆነ ፖለቲካ ማካሄድ አይቻልም ነበር። ስለዚህም የሶስተኛውን ዓለም አገሮች የአንዳንድ የኢንዱስትሪ ምርት ተጠቃሚ በማድረግና አንዳንድ መለስተኛ ግን ደግሞ ለዕድገት የማያመቹ ኢንዱስትሪዎችን በመትከል የድሮው የስራ ክፍፍል በሌላ መልክ ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ መመቻቸት ነበረበት። ይህንንም ለማድረግ በአንድ በኩል ከነፃ ገበያ በስተቀር የሰውን ልጅ ነፃ ሊያወጣው የሚችለው ሌላ አማራጭ መንገድ እንደሌለ መሰበክ ነበረበት። በየትምህርት ቤቱ እየተዘጋጁ የታደሉት የኢኮኖሚክስ መጽሀፎች የዚህ አንደኛው ገጽታ ናቸው። ይሁንና እነዚህን ለትምህርት ቤት ማስተማሪያ የተዘጋጁ የኢኮኖሚክስ መጽሀፍቶችን ላገላበጠ ፣ አንድም ቦታ በአንድ በኩል የካፒታሊሰት አገሮች የተጓዙበትን ጠመዝማዛ መንገድ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በአንድ አገር ውስጥ ስልጣኔና ህብረተሰብአዊ ለውጥ እንዴት ነው ሊመጣ የሚችለው ብሎ የሚያስተምርና አዲሱ ትውልድ ታሪካዊ ተልዕኮ እንዲኖረው የሚያደርግ አልነበረም። አይደለምም። በንጹህ አበስትራከት ቲዎሪ ላይ የተመረኮዘው ትምህርት ይበልጥ ለዕድገት ተቀናቃኝ ነበር ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። የአገራችንን የዕድገት ደረጃ

ተረድተን ወደ ፊት ምን ምን እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸውና አጠቃላይና ሁሉ-ገብ ዕድገት ሊመጣ እንዴት እንደሚቻል በፍጹም ለማሳየት የሚችል የትምህርት ስርዐት አልነበረም። አይደለምም። ዛሬ ካለብዙ ምርምር ልንገነዘብ የምንችለው በአብዛኛው የሶስተኛው ዓለም አገሮች የሚታየው የኢኮኖሚና የማህበራዊ ሁኔታ ይህንን ሀቅ ነው የሚያረጋግጠው። ከዕድገት ይልቅ ፀረ-ዕድገት። ከብልጽግና ይልቅ ድህነት። ይህም የትምህርቱ ውጤት እንደሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም የአንድ አገር ዕድገትም ሆነ ፀረ-ዕድገት የዚያው የአንድ አገር የትምህርት ነፀብራቅ ነውና።

ይህ ካለማወቅ ፣ በአፄ ኃይለስላሴ አገዛዝ የውጭ ኃይሎች በአገራችን ጣልቃ ገብተው እን ዲፈተፍቱ የተቀደደላቸው መንገድ ባለፉት ሃምሳ ዐመታት ስኑ-ልቦናው የተሰለበና ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል ብቅ እንዲልና ውድ እናት አገራችንን በተለያየ መንገድ እንዲዋጋ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል ማለት ይቻላል። ከላይ እንዳየነው ከቢሮክራሲው በአሻገር ፣ ሀይማኖትንና ባህልን አስታከው የውጭ ኃይሎች የአገዛዙን ደካማ ጎንና አርቆ አለማሰብ ተጠቅመው የአገራችንን የክርስትናም ሆነ የእስልምና ሀይማኖት የሚቀናቀኑና እንደ ኃይልም ሆነው ወጥተው የህብረተሰቡን አወቃቀር እንዲረብሹ የተቋቋሙት ሚሺነሪዎች ተግባራቸው የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ዕውነተኛ አማኝ እንዲሆን ማድረግ ሳይሆን ስራ የሚጠላ ፣ ፈዛዥና አገሩን ገልጦ ለውጭ ኃይል በርግጎ የሚሰጥ ፣ ከዚያም ባሻገር በአንዳንድ ቦታዎች ኢትዮጵያዊነቱን ክዶ ወደ አመጽ ሊሸጋገር የሚችል ጥራዝ ነጠቅ ኃይል ለማፍራት ነው። እንደዚህ ዐይነቱ በተለይም በወለጋ አካባቢ ጎልቶ ሲታይ ፣ ለዚህ ዋናው ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል ብቅ ማለት የጀርመን ሚሺነሪዎች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።እየተጫወቱም ነው። በስድሳዎቹና በሰባዎቹ ሀዘል ብላት የሚባል ጀርመናዊ የሆነ ፕሮቴስታንት ቄስ ነኝ ባይ ፣ ዋናው ተግባሩ ግን የስለላ ስራ ማካሄድና እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮችን ለማዳከም ወይም ደግሞ ለመበታተን ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችን ሲያደራጅ እንደነበር የታወቀ ነው። አሜሪካንም እንደዚሁ ልክ ማዕከለኛውና ላቲን አሜሪካ ውስጥ ሲያደርግ እንደነበረው ኢትዮጵያም ውስጥ በተለይም ወጣቱ በሀይማኖት እንዲታቀፍና ነገረ-ዓለሙን ትቶ ብሄራዊ ግዴታውን እን ዳይወጣ ለማድርግ የውስጥ ለውስጥ ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጊቱን ሲያካሂድ እንደሰነበተና እነ አቶ መለስ ዜናዊም ስልጣን ከወጡ በኋላ የልብ ልብ ተሰምቶት ህዝቡ ከጎሳ አልፎ በሀይማኖት ተከፋፍሎ ወደ እርስ በርስ ጦርነት እንዲያመራ ያልሞከረው ድርጊት እንደሌለ ነገሩን የተከታተለ ሊገነዘበው ይችላል።

ወደ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንመጣ ፣ በአፄ ኃይለስላሴ አገዛዝ ዘመን በ1950ዎቹ የተነደፉትንና ተግባራዊ የሆኑትን ፖሊሲዎች ዕውነተኛ የኢኮኖሚ ዕድገትን ያለካተቱና በፍጹም ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ ማበብና ህብረተሰቡ በጸና መሰረት ላይ እንዲቆም ሊያደርጉት የሚችሉ አልነበሩም። ፖሊሲውን ጠጋ ብለን ስንመረምር በጊዜው የነበሩ የኢትዮጵያ ምሁሮች ከብዙ ጊዜ ምርምርና ጥናት እንዲሁም ይኸኛው ይሻላል በሚል ክፍጭት በኋላ ያፈለቁት ፖሊሲ ሳይሆን ፣ የውጭ ኃይሎች ግፊት እንዳለበት ወዲያውኑ መረዳት እንችላለን። ይህም የኢኮኖሚ ፖሊሲ ይበልጥ ጥቃቅን የፍጆታ ዕቃዎችን በማምረት ላይ ያተኮረና የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ፍላጎት ብቻ የሚያረካ እንደነበረ ጥናቶች ያመለክታሉ። በመጀመሪያው ፣ ኢንዱስትሪዎቹ ያረጁ ነበር። ሁለተኛ ፣ በአገራችን ተመራማሪዎች አገር ቤት በሙከራ የዳበሩና ለአገራችን እንዲስማሙ ሆነው የተመረቱ አልነበሩም። ሶስተኛ ፣ ቀጥታ ከውጭ መምጣታቸው ከሳይንስ ምርምር ጋር የተያያዙ አልነበሩም። ለአንድ አገር የቴክኖሎጂ ዕድገት የሚያስፈልገው የምርምርና የሙከራ እንዲያም ሲል ውጤቱን በኢን ዱስትሪ መልክ አቀነባብሮ መጨረሻ ላይ ወደ ሙሉ ስራ እንዲሰማራና ምርትን እንዲያመርት የሚደረግ ሂደት በአገራችን በፍጹም አልተለመደም። አራተኛ ፣ ኢንዱስትሪዎቹ በጥሬ ሀብትም ሆነ በአጠቃላይ ኢንዱስትሪዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉት መለዋወጫዎች በሙሉ ከውጭ ነበር የሚመጡት። በዚህም ምክንያት ኢንዱስትሪዎች ሲበላሹ የመለዋወጫ ዕቃ እጥረት በሚኖርበት ጊዜ የምርት ሂደት ይቀንሳል ወይም ይገታል። አምስተኛ ፣ የተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ገዝቶ ስለሚጠቀም ኢንዱስትሪዎቹ በሙሉ መጠናቸ/ካፓሲቲ/ ለማምረት አይችሉም ነበር። በዚህም ምክንያት የማምረቻው ዋጋ

ስለሚናር ገበያ ላይ ወጥተው የሚሸጡት ምርቶች ዋጋቸው ውድ ነው። ስድስተኛ ፤ ለአንድ የካፒታለሲት ኢኮኖሚ የሚያስፈልገው ወድድር/ኮምፐትሺን/ በፍጹም አልነበረም። ኢን ዱስትሪዎቹ የኦሊጎሎፖይ ባህርይ ነበራቸው ማለት ነው። ሰባተኛ ፤ ኢንዱስትሪዎቹ ከሌሎች ጥሬ ሀብትን ከሚያመርቱ የኢኮኖሚ መስኮች ጋር የተያያዙ አልነበሩም። በዚህም ምክንያት አንድን ጥሬ ሀበት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ የመለወጥ አቅማቸው የተወሰነ ነበር። ስለሆነም ሰፋ ላለ የገበያ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚያመቹ አልነበሩም። ስምንተኛ ፤ የአብዛኛዎቹ ኢን ዱስትሪዎች ማኔጀሮች የውጭ አገር ሰዎች ነበሩ። በጊዜው ኢትዮጵያውያን ማኔጀሮች በዝቅተኛ ደረጃ ተቀጥረው እንደሚሰሩ ጥናቶች ያመለክታል። በዚህም ምክንያት ኢን ዱስትሪዎቹ ምን ማምረት እንዳለበቸው ፤ ለማን እንደሚመረቱና በምንስ ዐይነት ሁኔታ መደራጀት እንዳለባቸው የሚወስኑት የውጭ ማኔጀሮችና የበላዮቻቸው ናቸው ማለት ነው። ዘጠነኛ ፤ የስራ መስክ ለመክፈት ያላቸው ዕድል በጣም ዝቅተኛ ነበር። በተለይም በ1950ዎቹና 60ዎቹ ስራ ለመፈለግ ወደ ከተማ ለሚመጣው ህዝብ በቂ የስራ መስክ ለማዘጋጀት ባለመቻሉ እነዚህ ሰዎች የግዴታ ወደ አልባሌና ህብረተሰቡን ወደ ማይጠቅሙ ስራዎች እንዲሰማሩ መገደድ ነበረባቸው። ኩሌነት ፤ ማጅራት መችነት ፤ ሴተኛ አዳሪነት ፤ ጫማ በመጥረግ መተዳደር ፤ የዚህ ያልተሰተካከለና ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ ውጭ የሆነ የኢንዱስትሪ ተከላ ውጤት ነው ማለት ይቻላል። ይህ ዐይነቱም የኢኮኖሚ ፖሊሲ በከተማዎች አለማደግ ፤ በባህል አለመዳበር ፤ ሀብትን ከገጠር እየመጠጡ ወደ ጥቂት ከተማዎች በተለይም ደግሞ አዲስ አበባ ብቻ ላይ ማከማቸት የቱን ያህል በአገራችን ዕድገት ላይ አሉታዊ ውጤት እንዳመጣና የህብረተሰባችንን የወደፊት ጉዞ መወሰን እንደቻለ መገንዘቡ ከባድ አይሆንም።

በአጠቃላይ ስናይ አፄ ኃይለስላሴና አገዛዛቸው የተከተሉት የኢኮኖሚ ፖሊሲ በጊዜው በእነ ዐለም ባንክ የተደገፉና በአሜሪካንና በግብረ አበሮቿ ቡራኬን ያገኙ ፖሊሲዎች እንደሆኑ መረዳቱ ቀላል አይደለም። በጊዜው አሜሪካንም ሆነ ግብረ አበሮቿ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ሌላ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተደገፈ አገሪቱን ሊያዳርስና የዕውነተኛ ዕድገት መሰረት የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዳይነደፍና ተግባራዊ እንዳይሆን ያገዱትና ያሳሳቱት ፤ ለአንድ አገር እንደ አገርና እንደ ህብረተሰብ ሆኖ መዳበርና ተከታታይነት እንዲኖረው ማድረግ ሳይን ስና ቴክኖሎጂ መሰረታዊ ጉዳዮችና ለማንኛውም አገር ጤናማ ዕድገት አስፈላጊ መሆናቸውን በመገንዘባቸው ነው። ስለሆነም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዳያድግና እንዳይስፋፋ ሻጥር መስራት ፤ ሲያስፈልግ ደግሞ ወደ መንግሰት ግልበጣ እንደሚያመሩ በብዙ አገሮች የታየ የታሪክ ክስተት ነው። የፕሬዚደንት አሌንደን ሁኔታ ማጤን ብቻ በቂ ነው። ለምሳሌ አሜሪካም ሆነ ግብረ አበሮቹ ለእኛ የሚያስቡ ከሆነ ለምን በአስራ ስምን ተኛውና በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በአገሮቻቸው ተግባራዊ የሆነውን የመርከንታሊዝም ሆነ በእነ ሀሚልተን ዘመን አሜሪካ የተከተለውን የማኑፋክቱር የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንድን ከተል ምክር አልሰጡንም ? ባንክ በአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የሚኖረውን ሚና ማዕከላዊ ቦታ በመስጥት በዝቅተኛ ወለድ ላይ የተመሰረተ የክሬዲት ፖሊሲ እንዲካሄድ ለምን ምክር አልሰጡንም ? በተጨማሪም ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ብዙ የኢን ዱስትሪ አገሮች የተከተሉትን የማርሻልንና ሀብትን የማንቀሳቀስ/ሞቢላይዝ/ አስፈላጊነት ፖሊሲ እንደ ምክር አቅርቦ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች የኢንዱስትሪ ዕድገት ጎዳና እን ዲከተሉ አላደረጉም ? ይህንና ሌሎችን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮችን የማዳከም ስትራቴጂ ስንመለከት የምንደርሰበት መደምድሚያ አንዳንዶች እንደሚሉት አሜሪካንም ሆነ ግብረ አበሮቹ የአገራችንን ዕውነተኛ ዕድገት የሚፈልጉ ሳይሆን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ባለቤት እን ዳንሆንና እዚያው ቀጭጨን እንድንቀር ነው። ደግሞም በታሪክ እንደታየው አንድ አገር የሌላውን አገር ዕድገትና ብልጽግና ይሻል ብሎ ግትር ብሎ ካለምንም ሳይንሳዊ መረጃ ለመከራከር መሞከር አጉል ጭፍንነት ብቻ ሳይሆን የህብረ-ብሄርን አገነባብ ታሪክም አለመገንዘብ ነው።

ከዚህ ስንነሳ ፤ ከረጅም ጊዜ ጅምሮ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ አሜሪካንን የኢትዮጵያ ወዳጅ አድርጎ ለማቅረብ የሚደረገው ሙከራና ፤ አሜሪካም የኢትዮጵያን ዕድገት እን

ደሚፈለግ ማሰተጋባቱ የቱን ያህል ሳይንሳዊና የታሪክ መሰርት የሌለው መሆኑን መረዳቱ ከባድ አይሆንም። በተለይም የአንድ ህብረተሰብ ዕድገት ምን መልክ መያዝ እንዳለበትና የካፒታለስት ኢኮኖሚ መሰረቱ ምን እንደሆነ ለመገንዘብ የማይፈልጉ ኢትዮጵያውያኖች ፣ በተለይም ደግሞ የአንድ አገር ዕድገት በተራ ዝናና በጸሎት ብቻ የሚመሰርት የሚመስለቸው የዋህ ኢትዮጵያውያን የሚያስተጋቡት ፀረ-ሳይንስና በመሰረቱ ፀረ-ኢትዮጵያ ቅስቀሳ ለአገራችን በሚበጀው መሰረታዊ የቲዎሪ ጥያቄ ላይ እንዳናተኩር አግዶናል። እኛው እራሳችን በአንድ በኩል ኢትዮጵያን እንወዳለን ፤ በሌላ ወገን ደግሞ የአገራችንን ውድቀት እን ደምናዘጋጅ ለብዙዎቻችን ግልጽ አልሆነም። ይህ በተለይም በውጭ ኃይሎች ላይ ያለን አመለካከት እስካልተለወጠና ሁኔታውን በደንብ እየመረመርን እስካልተጓዝን ድረስ የአገራችን ሁኔታ የዛሬ ሁለት መቶ ዐመትም ከመቃብር ተነስተን ስንመጣ በባሰ ሁኔታ እንደሚጠብቀንና እንደምናየው መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህንን የምለው ካለምክንያት አይደለም። ዛሬም እንደ ትላንትናው አብዛኛው ቁጭ ብሎ የማጥናት ፣ የመከራከርና ሌላውን የማስተማር ፍላጎት የለውም። የብዙዎቻችን ችግር አሁንም የኃይል ሚዛንን መጠበቅ በሚለው አጉል ፖለቲካ ላይ ያተኮረ እንጂ በራሳችን ተማምነን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ባለቤት እንዴት መሆን እን ደምንችል ስንረባረብ አንገኝም።

<u>የውጭ ኃይሎች ፣ በተለይም የአሜሪካን ሚናና ተጽዕኖ በአብዮቱ ወቅት</u>

እንደሚታወቀውና አንዳንድ ስለኢትዮጵያ አብዮት ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያለቸው ምሁራን ስለ አገዛዙ መውደቅ ሲጽፉ ፣ ብዙ ነገሮች ተደማምረው በድሮው ሁኔታ ኢትዮጵያን ለማስተዳደር እንደማይችልና መውደቅም ግዴታው እንደነበር ያረጋግጣሉ። በመጀመሪያ የአገሪቱ የኢኮኖሚ መሰረትና የማህበራዊ ሁኔታ የምርት ኃይሎች እንዳያድግ አንቆ በመያዝ የኢትዮጵያን ህዝብ ወደ ባሰ ድህነት እየገፈተረ መጣ። የፊዩዳሉ ኢኮኖሚና እጅግ ተቆን ጽሎ የገባው የገበያ ኢኮኖሚ በቁጥር እየጨመረ ለመጣው ህዝብ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማህበራዊ ፍላጎቱን ሊያሟላለት አልቻለም። የስራ አጥ ቁጥር መብዛት ፣ የማህበራዊ ሁኔታ መመሰቃቀልና የአገሪቱ ኢኮኖሚ በተዝረከረከ መሰረት ላይ መጓዝ የአገዛዙ ድክመት እን ደሆኑ በጊዜው የኢትዮጵያን ሁኔታ ለተከታተለ መረዳት ይቻላል። በዚህ ላይ የወሎው ርሀብና በኋላም እ.አ በ1973/74 በካፒታሊሰት አገሮች የታየው የኢኮኖሚ ቀውስና የዘይት ዋጋ መወደድ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ሁኔታ ተጽዕኖውን እንዳሳደረ የማይካድ ሀቅ ነው። በቡናና በአንዳንድ የጥራጥሬ ሀብት ላይ የተመካው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በቀላሉ ለእንደዚህ ዐይነቱ ዓለም አቀፍ አጠቃላይ ቀውስ መጋለጡ የሚያስደንቅ ነገር አልነበረም። ምንም ሳይንሳዊ መሰረት የሌለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ "አፍንጫ ሲመታ ዐይን ያለቅሳል" እንደሚባለው አነጋገር መፈረካከስ ጀመረ። አገዛዙም የአገሪቱን ኢኮኖሚ መሰረት ለማሲያዝ ምንም ዐይነት በሳይንስ የተፈተነ መሳሪያ ስላልነበረው ፣ "በቡሐ ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ የቤንዚን ዋጋ እንዲጨምር በማድረግ በመቀጣጠል ላይ ባለው የህዝብ ብሶት ቤንዚን በማርከፍከፍ ሁኔታውን አባባሰው። እነዚህ ሁኔታዎችና በወታደሩ ውስጥ የተነሱት የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄዎችና የኋላ ኋላም ወደ ሌላ ያመሩት መሰረታዊ የአስተዳደርና የአገዛዝ መሻሻሎች አገዛዙን አናጉት። ያ በጸና መሰረት ላይ የተገነባ ይመስል የነበረው አስፈሪው የአፄ ኃይለስላሴ አስተዳደር በዚህ ቀስ በስ እያለ በተቀጣጠለ እሳት ፊት መብረክረክና መፈራረስ ጀመረ። እንዳንዶቹ ለማሰመን እንደመሚሞክሩት ለኢትዮጵያ አብዮት ወይም ለአገዛዙ መወደቅ ምክንያት የተማሪው ዕብደት አልነበረም። በእርግጥ ግን የተማሪው እን ቅስቃሴ ያነሳቸው የዲሞክራሲና የመሬት ለአራሹ ጥያቄዎች መሰረታዊ ጥያቂዎች በመሆናቸው ለአገዛዙ በፍጥነት መውደቅ አስተወጽኦ አድርገዋል ማለት ይቻላል። ከዚህ ባሻገር የተማሪው እንቅስቃሴ በጊዜው በሰፊው ያላጤነውና ያልተዘጋጀበት ፣ ሁኔታው ወዴት እንደሚያመራና በምንስ መልክ መቆጣጠርና የተረጋጋ ሁኔታ በመፍጠር መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ይቻላል በሚለው ላይ ነበር። እንሚታወቀው በነዚህ ነጥቦች ላይ ከመጀመሪያውኑ

ጥሩ የቤት ስራ ባለመሰራቱ መከሰት የሌለበት ሁኔታ ተፈጠረ። ይህ ምናልባት የአገራችን የታሪክ ዕጣ ሆኖ ሊሆን ይችላል።

ለማንኛውም ፣ የአፄ ኃይለስላሴ አገዛዝ ሁኔታውን ለመቆጣጠር ያልተዘጋጀውን ያህል የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምም ያላሰበው ሁኔታ ተፈጠረበት። በመጀመሪያ እ.አ ከ1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ አሜሪካን በተለይም በውጭ ንግዱ ላይ የበላይነቱን በጀርመንና በጃፓን እየተነጠቀ የመጣበት ወቅት ነበር። የንግድ ሚዛኑም በዚሁ ዘመን በከፍተኛ ደረጃ የተናጋበት ጊዜ ነበር። ስለሆነም በብሬተንስ ውድስ ስምምነት መሰረት ብዙ ወርቅ ወደ አውሮፓ እየፈሰሰ የመጣበትና የአሜሪካንም የወርቅ ክምችት እየተሟጠጠ የመጣበት ጊዜ ነበር። ስለሆነም እ.አ በ1971 ዓ.ም በፕሬዚደንት ኒክሰን የሚመራው አስተዳደር ፣ አሜሪካን ምዕራብ አውሮፓ የተከማቸውን ዶላሩን ከእንግዲህ ወዲያ ወደ ወርቅ እንደማይለውጥ ያስታውቃል። ይህ ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያው ወቅት በቤሬተንስ ውድስ ስምምነት በደረሱት አገሮች መሀከል የመጀመሪያው መሻከርና በተለይም በኢኮኖሚ መስክ የኃይል ሚዛን መለወጥ የታየበት ወቅት ለመሆኑ የተረጋገጠበት ጊዜ ነው። በተጨማሪም በ1973 ዓ.ም እንደዚሁ የብሬተንስ ውድሱ ስምምነትን በማፍረስ ከእንግዲህ ወዲያ በዴማንድና በሰፕላይ ላይ የተመሰረተ የከረንሲ ገበያ መፈጠር እንዳለበት ፣ ቀደም ብሎ የነበረው ቋሚ የከረንሲ ልውውጥ(ፊክስድ ኤክስቼንጅ ሬት/ ቦታ እንደሌለው ዩኒላተራል የሆነ እርምጃ በአሜሪካን ይወሰዳል። ይህ ሁኔታ በአጠቃላይ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ዕድገትና አረማመድ ላይ አዲስ ሁኔታ ይፈጥራል። ከዚህ በተረፈ በቤትናም ጦርነት የተወጠረው አሜሪካን ብዙ ዶላር በማተሙ የዶላርን ዋጋ ዝቅ እያደረገው በመምጣት እንደ ጀርመን ላሉ የውጭ ከረንሲዎች ጥንካሬ ሰጥቶአቸዋል። ከዚህም ባሻገር በሚሊታሪ ሳይንስና በኢንፍርሜሽን ቴክኖሎጂ ላይ ብቻ ያተኮረው የአሜሪካ ኢኮኖሚ ፣ በማሽን ቴክኖሎጂ ላይ አትኩሮ አድርገው መኪናዎችን ና ሌሎች የማሽን ውጤቶችን ለሚያመርቱት ለእነጃፓንና ጀርመን ሜዳውን እየለቀቀ እን ዲመጣና የውስጥ ገበያውም በእነዚህ አገሮች ምርት እየተወረረ እንዲመጠ ተገደደ። እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮችና አሜሪካንም በውጭ ፖሊሲው ይበልጡኑ እየተጋለጠና እየተጠላ በምምጣቱ ሳይሰበው የተከሰተው የኢትዮጵያን አብዮት በአንዳች መልክ ለመግታት ተሳነው። በቀጥታ ሊጋፈጥ ያልቻለውን የኢትዮጵያን ህዝቦች እንቅስቃሴ በሌላ መልክ ማኮላሸት ነበረበት።

በመጀመሪያ በስለላ ሙያ የሰለጠኑ ኢትዮጵያኖችን በማስገባት አይ አገዛዙን በቁጥጥር ስር ማድረግ ነበረበት ፤ ካሊያም ሁኔታው ወደ ርስበርስ ጦርነት አምርቶ ኢትዮጵያ ሌላ ፈተና ውስጥ ወድቃ የተረጋጋ አገዛዝ እንዳይፈጠር ማድረግ ነበረበት። የመጀመሪያ በጊዜው ከሸፈበት። አሜሪካዊ መስለው በአሜሪካን የስለላ ማሺን ውስጥ ይሰለጥኑ የነበሩ ከሀዲ ኢትዮጵያውን መግቢያ ቀዳዳ በማጣታቸው ለጊዜው የህዝቡን የዲሞክራሲና የመሬት ለአራሹን ጥያቄ ሊያፍኑ አልቻሉም። ወደ ውስጥ ግን እንዴት አድርገው ሁኔታውን እን ደሚቀለብሱ ዝግጅት ያደርጉ እንደነበር በኋላ የተከሰተው የደም መፋሰስ በራሱ በቂ ማስረጃ ነው። ብዙ ኢትዮጵያውያን ፣ በተለይም የደርግ አገዛዝን ካለብዙ ውጣ ውረድ በጭፍን የሚጠሉ ከመጀመሪያውኑ ወታደሩ ደም የጠማውና ፋሺሽት እንደሆነ እንዲያውም ከኢትዮጵያ አብራክ እንዳልተፈጠረ አድርገው በህዝቡና በወታደሩ መሀከል የማያስፈልግ መቃቃር እንዲፈጠር አድርገዋል። በጊዜው ረጋ ብሎ ደርግ ህዝባዊና ዲሞክራሲዊ መስመር እንዲከተል ምክር ከመስጠት ይልቅ በመሳደብና በማሾፍ እንዲሁም ፋሺሽት የሚል ቅጽል በመስጠት የማያስፈልግ ቅራኔና ደም መፋሰስ እንዲፈጠር አደረጉ። በዚህ ላይ ደርግ የወሰደው በተለይም ፊዩዳሉን የሚያሰቆጣ የመሬት ፖሊሲና ንዑስ ከበርቴውን የሚያዳክም እርምጃ በህዝብ ዘንድ እንዲጠላ አደረገው። የደርግ ፖሊሲ ግልጽ አለመሆን ፣ የፖለቲካ ብስለት እጥረትና በተለይም ደግሞ ተራማጅ ነኝ ከሚለው የሚወረወረው መፈክርና ዝልፊያ ፣ እንዲሁም በራሱ በተራማጁ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ ያለው ሽኩቻ የኢትዮጵያን ህዝቦች የስልጣኔ ፍላጎት ለሚያዳክሙ ኃይሎች ሁኔታውን እያመቻቸው መጣ። ፊዩዳል እየተባለ ከሚወነጀለው ባሻገር ኢትዮጵያ በስንት መከራ ያፈራቻቸው አገር ወዳድ ምሁራን ፣ ዛሬ ማንም ተተኪ የማይገኝላቸው ፣ ኢትዮጵያን የምሁር አልባ ለማድረግና እን

ዲያም ሲል የበሰለ የከበርቴ መደብ እንዳይፈጠር ለሚሹ ኃይሎች ሁኔታው ተመቻቸ። የፊዩዳሉ መደብ ፣ በስንት መከራ ሀብት ያፈራው ንዑሰ ከበርቴ መደብና በቀላሉ ተተኪ ሊገኝላቸው የማይችል ምሁራን ባለማወቅ እንደጠላት እየተቀነጠሱ አለፉ። በዚህ ሁኔታ የአሜሪካንም ሆነ ሌላው የምዕራብ ኢምፔሪያሊዝም ኢትዮጵያ የኮሙኒሰት ጉያ ውስጥ ወድቃለችና ፈልቀቅን ማውጣት አለብን በሚል ፕሮፓጋንዳ በመሰረቱ በኢትዮጵያ ህዝቦች የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ዘመቻ ማካሄድ ጀመሩ። ደርግን ሊቋቋሙ የሚችሉ ኃይሎችን ሁሉ በማቴሪያልም ሆነ በሞራል መደገፍ ተያያዙት። በዲሞክራሲና በሊበራሊዝም ስም የኢትዮጵያን ኮንትራዎች ማደራጀት ጀመሩ። ይህ ብቻ ሳይሆን ሶማሌ ቀጥታ ኢትዮጵያን ስትወር መሳሪያ በማቀበል አገራችንና ህዝባችን እንዲደሙ አደረጉ። ከዚህም ባሻገር በማርክሲዝም ሌኒንዝም ስም የሚታሙት የነፃ አውጭ ተብዬዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአሜሪካን ድጋፍ እንደነበራቸው ብዙ ፍንጮች ያመለክታሉ። ዋናው የደርግን አገዛዝ ማናጋትና ቢቻል ፕሮ አሜሪካን መንግሰት መመስረት ፣ ይህ ካልተቻለ ደግሞ አጠቃላይ የእርስ በርስ ጦርነት እንዲቀጣጠል ማድረግ ነበር የእነ አሜሪካን ተግባር።

እዚህ ላይ ይህንን የማትተው የኋላ የኋላ እጅግ አረመኔያዊ የሆነውን አገዛዝ በመደገፍ አይደለም። እጅግ የተወሳሰበውን የኃይል አሰላለፍ ለማመልከትና በቀላሉ በማይሆን ርዕዮተ ዓለም እየታለልን የአገራችንን ውድቀት እንዴት እንዳፋጠን ለማሰየት ብቻ ነው። በተጨማሪም በቅጡ የዓለም አቀፍን የፖለቲካ ሂደት ለመገንዘብ ያለመቻልና በአለፉት 500 ዓመታት የተካሄደውን የህብረ-ብሄር አወቃቀር ታሪክ ካለመገንዘብ የተነሳ የቱን ኃይል እንደኛ ያለው ታሪክን እያገናዘበ አገሩን ለመገንባት የማይችል ትውልድ የውጭ ኃይሎች ሰለባ በመሆን አገሩን እንደሚያፈራርስ ለማመልከት ብቻ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በጊዜው ተራማጅ ነኝ በሚለው ኃይል በኩል አንዳች ዐይነት ስምምነት ተደርጎ ከደርግ ጋር አብሮ ቢሰራና ፀረ-አብዮት እያሉ በማሰበርገግ ሳይሆን ህዝቡን በማስተማር አገሪቱንና ህዝቡን ሊጠቅሙ የሚችሉ እርምጃዎች ተግባራዊ ቢሆኑ ኑሮ አብዮቱ ከቁጥጥር ውጭ ሊወጣ አይችልም ነበር። የፖለቲካ ብስለት ጉድለት ፣ ጥድፊያና የማያስፈልግ ሽኩቻ የቱን ያህል በመሀከላችን አለመግባባት እንደፈጠረና ለዛሬው ሁኔታ የበኩሉን አስተዋፅዎ እንዳደረገ ለማመልከት ብቻ ነው። ሌላው በደንብ መገንዘብ የሚገባን ፣ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ የኢኮኖሚና የህሊና አወቃቀር በደንብ ሳይመረምሩ አንድን የህብረተሰብ ክፍል በጅምላ ወስዶ ፋሺሽት ወይም አድሃሪ የሚያሰኝበት ምንም ምክንያት አልነበረም። ስለሆነም የማያስፈልግ ሽኩቻዎች ውስጥ በመግባት እንዋጋለን ለምንለው ኢምፔሪያሊዝም ሰለባ ሆንን። በዚያው መጠንም የውስጥ ለውስጥ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ኢትዮጵያን እጁ ውስጥ የሚያገባበትና የሚያሸበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተያያዘው። ለዚህ ደግሞ አብዮቱ ያልዳሰሰውና ኋላ ጓድ እየተባለ ኢሰአፓ ውስጥ የተሰገሰገው የሚሊታሪና የሲቪል ቢሮክራሲ ጥሩ ኃይል ነበር። የዛሬው የወያኔው አገዛዝም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በአንዳንድ ከሀዲ ቢሮክራቶች ነው መንገዱ እየተጠረገለት እንዲገባና አገራችንን እንዲያምስ ሁኔታው የተዘጋጀለት። በተወሰኑ ኃይሎች ያለማወቅና ለስልጣን መስገብገብ እንዴት አድርጎ አንድ አገር እንዲፈርስ ሁኔታዎችን ማዘጋጀት እንደሚቻል ለማመልከት ነው። ይህም ሆነ ያ ተባለ እኛ ኢትዮጵያውያን ለምን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መሳሪያ ለመሆን እንደበቃን በፍጹም ሊገባኝ አይችልም። ለምን ዐይናችን ታውሮ በአገራችንና በዚያ ስልጣኔ በጠማው የዋህ ህዝብ ላይ ጦርነት እንዳወጅንበትና መንገዱንም አገራችንን ምስቅልቅሏን ለሚያጠፉ ድርጅቶችም ሆነ አገሮች እያዘጋጀን እንደምንሰጥ ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነው።

በኢትዮጵያ አብዮት ወቅት እንደዚያ የርስ በርስ እልቂት የጦፈው በመሰረቱ የተለያየ አመለካከት ባላቸው በግራ ኃይሎች የተቆሰቆሰ ነው ቢባልም ለወጣቱ ደም መፍስስ አሜሪካን ም ተጠያቂ እንደነበረ የማይካድ ሀቅ ነው። በተለይም ስልጣን ለመያዝ ያሰፈሰፈውም ሆነ ዕድሉን በአሜሪካን ቡራኬ ላይ ያደረገው የተደናበረ ኃይል የማቴሪያልም ሆነ የሞራል ዕርዳታ የሚያገኘው የኢትዮጵያን አንድነትና ጥንካሬም ከሚቀናቀነው ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ነው። እ.አ በ1977 ዓ.ም የቃኘው የጦር ሰፈር ቢዘጋምና በደርግና በአሜሪካን መሀከል ያለው ግኑኝነት እየሻከረ ቢመጣም በርዕዮተ ዓለም ሆነ በብዙ

የአሰራርና የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ቴክኒክ አገዛዙ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ዘመናዊ የሚመስል በመሰረቱ ግን ፀረ-ዕድገት የአሰራር ዘዴን ሲከተል ነው የከረመው። በማርክሲዝምና በሶሻሊዝም ስም ብዙ ልፈፋ ቢካሄድም ይህ ከፖለቲካ አደረጃጀት ያላለፈ ፤ የኋላ ኋላ እንዳየነው የራሱን ልዩ ክስተት የፈጠረና ለዕድገት ማነቆ የሆነ በአንድ ፓርቲ ጥላ ስር የተቀነባበረ አምባገነናዊ አስተዳደርንና የጭቆናን መሰረት የዘራጋ በብዙ ኋላ ቀር ኢኮኖሚዎች የተከሰተ ዐይነት ሁኔታ ነው በአገራችንም የተፈጠረው። በሌላ አነጋገር ከኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር የደርግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ- የሶሻሊዝም የኢኮኖሚ ፖሊሲ አለ የሚባል ካለ- ቢያንስ ሶቭየት ህብረትም ሆነ ሌሎች የምስራቅ አውሮፓ አገሮች በ1920ዎቹና ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ፕሪሚቲቭ የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ክምችት/ፕሪሚቲቭ ሶሻሊስት አኩሙሌሽን/ የሚባለውን በብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ላይ ያተኮረና ሰፊውን ህዝብ ለስራ የቀሰቀሰ ዐይነቱን ያልተከተለ በመሆኑ ሶሻሊስታዊ የሚያሰኘው አንዳችም ነገር አልነበረም። ማለት የሚቻለው የደርግ ፖሊሲ ከሞኔታሪም ሆነ ከንፁህ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አን ፃር ሲተነተን የአገሪቱን የሰውም ሆነ የማቴሪያል ሀብት በተጠና መልክ ሊያንቀሳቅስ ያልቻለ ግራ የተጋባ ፖሊሲ ነበር ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል።ይህም ሁኔታ የኋላ ኋላ ደርግ ሊወድቅ ሲል ባወጣው የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ሊታረም አልቻለም።ምክንያቱም የገበያው ኢኮኖሚ ይበልጥ የውጭ ኢንቬስተሮችንና የእነ አሜሪካንን ቡራኬ ለማግኘት የተነደፈ ፖሊሲ በመሆኑና የኢትዮጵያን ህዝቦች ብልጽግናና ዕድገት ያለካተተ እንዲሁም በሳይንስና በቴክኖሎጂ መርሆች ላይ ያልተመሰረተ ፖሊሲ ስለሆነ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። ለዚህም ነው ከ17 ዐመት የደርግ አገዛዝ በኋላ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከእጅ ወደ አፍ /ሰብሲስተንስ/ ብቻ በሚካሄድ የእርሻ የምርት ክንውንና በኢንፎርማል ሴክተር ላይ እንዲቀር የተገደደው።

ያም ሆነ ይህ ደርግ የወሰዳቸው ሶሻሊስታዊ የሚመስል እርምጃዎችና የማርክሲዝም ሌኒን ዝም እንካ ስላንቲሃ ንትርክ አሜሪካኑንም ሆነ የተቀረውን የምዕራቡን  ዓለም ፀረ-ኢትዮጵያ አቋሙን እንዲገፋበትና የውስጥ አርበኞችን በማደራጀት የእርስ በርስ ፍልሚያ እንዲካሄድ መንገዱን ጠርጎለታል ማለት ይቻላል። በጊዜው የአሜሪካንም ሆነ የሌሎች ፍርሀት ኢትዮጵያ ውስጥ ተከታታይነት ያለው ሶሻሊዝም ይመሰረታል ብለው በማሰብ ሳይሆን ፤ ይህ ዐይነቱ እርምጃ ብሄራዊ ስሜትን አዳብሮ የእነ አሜሪካንን የበላይነት የሚቀናቀን ለዕድገት የሚሆን መሰረት መጣል ይቻላል ብለው በመገመት ብቻ ነው። በአብዮቱ ወቅት የእነ አሜሪካን የውጭ ፖሊሲ በመሰረቱ ፀረ- ዕድገትና የፀረ ኢንዱስትሪ አብዮት እንጂ የሶሻሊዝም አብዮት ይመጣል ፤ መሰረት ይይዛል ብለው በመፍራት አልነበረም። ከዚህም በላይ የደርግ በሶቭየት ህብረት ጉያ ስር መውደቅ በአካባቢው ያለውን የኃይል አሰላለፍ መለወጥ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌላ አካባቢዎችም እየተዛመተ በመሄድ የአሜሪካንን የበላይነት የሚቀናቀን በመሆኑ አጥብቆ መዋጋትና አብዮቱን በዚህም በዚያም ብሎ ማክሸፍ ነበረበት።

እንዳየነው የደርግ መደናበር ፤ በነቃው ምሁር ላይ መዝመት ፤ የቢሮክራሲው አሻጥር ፤ በመሰረቱ ፀረ-ኢትዮጵያ ድርጊት ፤ በደርግ ውስጥ የነበረው ያልሰከነ የኃይል አሰላለፍ ፤ ፕሮ አሜሪካንና ፕሮ ሶቭየት ኃይሎች ፤ በደርግ አመራር ስህተት ፤ በተለይም አገር ወዳድና ጀግና መኮንኖችን ማግለል ወይም መምታትና በደንብ ያልሰለጠኑ ኃይሎች የጦር አመራሩን እን ዲይዙ ማድረግ ፤ የደርግ ካድሬዎች መባለግና ህዝብን ማስመረር ፤ ለሲ አይ ኤ መስመር መዘርጋትና አገዛዙ እንዲገረሰስ መንገድ ሲቀድ ፤ በዚያው መጠንም እንደ ወያኔ የመሳሰሉ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ሁኔታውን ተጠቅመውና በእንግሊዝና በአሜሪካን እየተረዱ ኢትዮጵያን ማዳከም ቻሉ። ወያኔና ሻቢያ እንደሚፎክሩት እነሱ የኢትዮጵያን ወታደር መቋቋም ስለቻሉና የተሻለም የጦር ስልት ስላላቸው አልነበረም በአሸናፊነት መውጣት የቻሉት ። ከዚህም በላይ ሻቢያና ወያኔ እራሳቸው ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ስለነበሩ በቀላሉ ኢትዮጵያንና የደርግን አገዛዝ ለማዳከም ይቀላቸው ነበር። በአፄ ኃይለስላሴም ሆነ በደርግ አገዛዝ ዘመን በስልጣን አካባቢ የተኮለኮሉና በልዩ ልዩ ኢንስቲቱሽኖች ውስጥ ተቀጥረው ይሰሩ በነበሩ አባሎቻቸው ወይም ደጋፊዎቻቸው  ይረዱና መረጃዎችን ያገኙ ስለነበር በቀላሉ አገዛዙን ለማዳከም ይችሉ ነበር። በታሪክ ውስጥ እንደታየውም የውስጥን ጠላት ለማሸነፍ በጣም አስቸጋሪ ነው። በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ-አብዛኛውን ጊዜ በጎሳ

በኩል የሚመጣ ጭቆናን- የወስጥ ጠላትን ለመደምሰስና በአሸናፊነት ለመወጣት ማንኛውም አገዛዝ ይከብደዋል። በተለይም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ጀምሮ የተከሰቱትና በየጊዜው እየተለዋወጡ የመጡት ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ሁኔታዎች ከውስጥ ለሚነሱ የፖለቲካ ችግሮችና አፈንጋጭ ኃይሎች ለአንደኛ ላለው የህብረ-ብሄርን አወቃቀር ላላጠናቀቀው አገር አስቸጋሪ ሁኔታን እንደሚፈጥርብን ነው። ስለዚህም የውስጥ ችግርንም ሆነ ከውስጥ የሚነሳ ብሄራዊ ነፃነትን ሊያናጋ የሚችል ጠላትን በኃይል ሳይሆን በፖለቲካ ብቻ ነው መፍታት የሚቻለው። ወደ ጦር ማምራትና ችግርን በሚሊታሪ ኃይል እወጣዋለሁ ማለት ሌላ ውስብስብ ችግር ውስጥ ነው የሚከተው። የደርግ አንዱ ችግርም ማንኛውንም የብሄረ-ሰብ አፈንጋጭ ኃይል እደመስሳለሁ ብሎ መነሳቱ ነው። እንዳየነው ይህ የትም አላደረሰም። የብሄረ-ሰብ ነፃ አውጭ ነን የሚሉ ኃይሎችን የባሰውኑ የአሜሪካንና የእንግሊዝ እንደዚሁም የጀርመን ጉያ ውስጥ እየከተታቸው አጠናከራቸው እንጂ።

## የወያኔ አገዛዝ የአሜሪካንና የእንግሊዝ ቅምጥ መንግስት ነው ።

በአለፉት አስራ አራት ዐመታት በተከተታይ የወጡትን ብዙ ጽሁፎች ለተመለከተና ግንዛቤ ውስጥ ላስገባ የወያኔ አገዛዝ በአፈጣጠሩ ማርክሲስት ድርጅት እንደሆና አወቃቀሩም ስታሊኒስታዊ እንደሆነ ነው። አልፌውም ወያኔ የሚያካሄደው የሶሻሊስት ኢኮኖሚክ ፖሊሲ በመሆኑ ለአገራችን የኢኮኖሚ ውድቀት ምክንያት ነው ብለው ይደመድማሉ። ለዚህ እን ደምሳሌ የሚሰጡት በተለይም መሬት አሁንም በመንግስት ቁጥጥር ውስጥ እንዳለና ለኢን ቬስትሜንት እንቅፋት እንደሆነና የገበሬውንም የማረስ ፍላጎት እንደቀጨው እንደምሳሌ ያቀርባሉ። እዚህ ላይ የኛ ክርክር ኢህአዴግ ወይም ወያኔ ማርክሲስት ነው ወይም አይደለም ፣ እስካሁን ተግባራዊ ሲያደርግ የቆየው የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ፖሊሲ ነው ወይስ አይደለም ብሎ ንትርክ ውስጥ ለመግባት ሳይሆን ብዙዎቻችን በኢህአዴግ የፖለቲካ ዕድገት ሂደት ውስጥ የታዩትን ክስተቶችና ለውጦች ግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባታችን ለምን የተሳሳተ የፖለቲካ ስልት መከተል እንደተገደድንና ኃይላችንንም እንዳባከንን ለመጠቆም ብቻ ነው።

ያም ሆነ ይህ ኢህአዴግ ማርክሲሲት ድርጅት ነው አይደለም ፤ ስለዚህም ነው አምባገነናዊ ሊሆን የበቃው ፤ ወይም የችግሩ ምንጭ ይህ አይደለም ብሎ ብዞዎችን ለማሳመን በጣም አስቸጋሪ ነው። በመጀመሪያ በማርክሲዝም ሆነ ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ ያለን ግንዛቤ በቂ ነው ብሎ ለመገመት በጣም ያዳግታል። በነገሩ በቂ ግንዛቤ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሰፊ ትንተና እስካላቀረቡልን ድረስ በዚህ በኩል ያለን ዕውቀት አነስተኛ ብቻ ነው ብሎ ከማለፍ በስተቀር ሌላ መደምደሚያ ላይ መድረስ ያስቸግራል። በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ የማርክሲስት ድርጅት ነው ከተባለ ለምን እ.አ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ በአገራችን ምድር የኒዎ-ሊበራል ወይም በእነ አይም ኤም ኤፍ የነፃ ገበያ እየተባለ የሚታወቀውን አገር አፍራሽ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ። ነገሩ ብዙ ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ነው። ሁለተኛ ፣ አንድ ድርጅት ይህንን ርዕዮተ-ዓለም እከተላለሁ በማለቱ የሚለካ ሳይሆን ፣ መለኪያው በተግባር የሚውስዳቸው እርምጃዎች ናቸው። ሶስተኛ ፣ የህብረተሰብ ሳይንስ አዋቂዎችም ሆነ የህሊና ሳይንስ ተመራማሪዎች ለማሳሰብ የሚፈልጉት የአንድ ድርጅትም ሆነ የግለሰብ ማንነትና ድርጊት የሚለካው በዚያ በአደገበት አካባቢ የቀሰማቸው ሁኔታዎችና የለመዳቸው የአኗኗር ስልቶች አስተሳሰቡንም ሆነ ድርጊቱን እንደሚወስኑ ነው። በተለይም ለአንድ ሰው የወደፊት ድርጊት ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ እስከ አምስት ዐመት ድረስ ያሉት የዕድሜ ጊዜያት ለአስተሳሰብ መታነፅ በጣም ወሳኝ ናቸው። በሌላ አነጋገር ትምህርት ቢማርምና ይህንን ሆነ ያኛውን ርዕዮተ-ዓለም አንግቤ እታገላለሁ ቢልም እስከዚህም ድረስ በአስተሳሰቡና በድርጊቱ እምብዛም ሊለወጥ አይችልም። ሊለወጥ የሚችለው ከፍተኛ የጭንቅላት ትግል ካደረገ በኋላ ነው። ይህ ቢሆን ኑሮ አፍሪቃ በተማሩ ሰዎቿ ይህን ያህል በደል ባልደረሰባት ነበር። በአገራችንም ሆነ በሌሎች አፍሪቃ አገሮች የተካሄዱትና የሚፈጸሙት ወንጀሎች በተራ ሰዎች ሳይሆኑ በምዕራቡ የትምህርት ስልት በሰለጠኑ ነው። ለዚህም ደግሞ በቂ ምክንያት

አለ። ለምሳሌ ፍሪድርሽ ሺለር የተባለው የድራማና የፍልስፍና ሊቅ ከብዙ ጊዜ ምርምርና የታሪክ ግንዛቤ እንዲሁም የፍልስፍና ጥናት በኋላ የደረሰበት ድምደማ በፖለቲካ ሂደት ውስጥ እንሳተፋለን የሚሉ ሰዎችም ሆነ በአንድ አገር ውስጥ የሚኖር ህዝብ የግዴታ ጭን ቅላቱ በጥበብ መታነጽ እንዳለበት ያሳስባል። ለዚህም ነው ዘ ኤስቴቲካል ኢዱኬሽን ኦፍ ዘ ሂዩማን ማይንድ የሚለውን ግሩም ጽሁፉን ያቀረበው። የሼክሰፔሪም ድራማ የሚያመለክተው የሰዎችን ተለዋዋጭ ባህርይ ፣ ደም መጣጭነት ፣ በአስፈላጊው ጌዜ ቆራጥ እርምጃን ለመውሰድ አለመቻልና አደገኛነት የሚያመለክት ትልቅ አስተዋጽዎ ነው። ይህም ጽሁፍ የመነጨው ሼክስፔዬር በንጉሳዊውና በባላባቱ መሀከል የነበረውን የተበላሸ ፖለቲካ በቅጡ ከተመለከተና ከተገነዘበ በኋላ የደረሰበት ድምደማ ነው። ከዚህ ስንነሳ አንድን ድርጅት ወይም ግለሰብ የምንለካው እሱ እንደዚህ ነኝ በማለቱ ሳይሆን ካደገበት የህብረተሰብ አወቃቀር በመነሳትና የቀሰመውን ትምህርት ግንዛቤ ውስጥ በመክተት የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በመገምገም ብቻ ነው። ለዛሬው የፖለቲካ ትግላችን ግን እዚህ ላይ ሰፊ ትንተና መስጠት አያስፈልግም። ጊዜውም አይደለም። የጽሁፉ መነሻ ወይም አርዕስት የምዕራቡ ዓለም በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ግምትና ፍላጎት ማሳየት እንደመሆኑ መጠን ፣ የኢህአዴግ አገዛዝ የምዕራቡ አሻንጉሊትና መጫወቻ መሆኑን ለማረጋገጥና ለዕውነተኛ ብሄራዊ ነፃነት የሚደረገው ትግል ምን መመስል እንዳለበት ለማመልከት ብቻ ነው።

የዛሬውን የወያኔ አገዛዝ ፖለቲካ ለመረዳት በአንድ በኩል የህብረተሰባችንን ህሊና አወቃቀርና በአለፉት ሃምሳ ዓመታት በስልጣኔ መልክ ወደ አገራችን የገባው ትምህርት ያሳደረብን ብሄራዊ ነፃነትን የሚሸረሽርና የሚያጎድፍ ትምህርት በደንብ መመርመር ይገባል። በሌላ በኩል ቀደም ብዬ በአወጣሁት ጽሁፍ ላይ ለማመልከት እንደሞከርኩት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ውስጥ ለውስጥ እነ መለሰ ዜናዊን በሲ አይ ኤ ጉያ ስር ለማምጣትና ጠቅላላለውን የኢትዮጵያ የፖለቲካና የህብረተሰብ አወቃቀር ለመበወዝ ከተተለመው የእነ አሜሪካን የውጭ ፖሊሲ ተነጥሎ ሊታይ በፍጹም እንደማይቻል ነው። ከዚህም በላይ እ.አ ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ እየተለወጠ የመጣው ዓለም አቀፋዊ ኃይል አሰላለፍ አዲሱ የአፍሪቃ ወጣት ዲሞክራቶች እየተባሉ ለሚጠሩት በመሰረቱ የእንግሊዝንና የአሜሪካንን ጂ ኦ ፖለቲካ ጥቅም ለሚያስጠብቁ ኃይሎች ለእነ መለስ ዜናዊ ፣ የሩዋንዳው ካጋሚና የዩጋንዳው ሙዘቬኒ መን ገድ የከፈተ ጥሩ አጋጣሚ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። እስከ 1989 ዓ.ም የነበረው የሁለት ኃያላን መንግስታት ፍጥቻ/ቢ ፖላሪዝም/ ወደ አንድ ወገን ሲያደላና ለጊዜው የአሜሪካን ኤምፔሪያሊዝም በአሸናፊነት ሲወጣ የቀድሞው የፕሬዚደንት ካርተር አማካሪ የነበሩት የፖለናዊው ተወላጅ ብርዜስኒሰኪ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ያወጡት የሶቭየት ህብረትን ተፎካካሪነት ማዳከምና በዓለም አቀፍ ደረጃ የአሜሪካንን ብቻኛ በላይነት አስፍኖ ስትራቴጂክ ጥሬ ሀብቶች ያሉባቸውን አገሮች ብቻ ሳይሆን መመለሻ የባህር መንገዶችንም መቆጣጠርና የተበላሸውን የአሜሪካንን ባህልና ርዕዮተ ዓለም ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እን ዲኖረው ማድረግ ተግባራዊ እየሆነ እንዲመጣ ዕድል አገኘ። ለዚህ ደግሞ ውስጥ ለውስጥ ሲያደባ የነበረው ከፊሉ የውህአት አካል በሲ አይ ኤ ጉያ ስር ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፋዊ የሲናርክስቲክ መዋቅር ውስጥ ገብቶ በመታሸት አገራችንን የውጭ ኃይሎች መጨፈሪያና ልዩ ዐይነት የአፓርታይድ ፖለቲካ የሚካሄድባት አገር ለማድረግ በቃ። እንደሚታወቀው ሲናርክሲዝም ልዩ የሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅግ በተወሳሰበ መንገድ የተደራጀ የሚሊታሪ-ኢንዱስትርና የፊናንስ ኦሊጋርኪዎች ውህደት የሆነና ብዙ የምዕራብን ፖለቲከኞች ፣ በተለይም ደግሞ የነፃ ገበያን ወይም የኒዎ ሊበራሊዝምን ርዕዮተ ዓለም የሚያራምዱ ኃይሎች ያካተተ ነው። ይህ ዐይነቱ ዓለም አቀፋዊ ኒዎ ፋሺሽት ኃይል በአሜሪካን ኢቫንጄሊስቶችና በኮንሰርቫቲቭ ድርጅቶች/ ቲንክ ታንክ ፎርሰስ/ እነ ኒዎ ስሚዝያንና ይህን የመሳሰሉትን ኢንስቲቱሽኖች ሲደገፍ ዋናው ዐላማው በዓለም አቀፍ ደረጃ ለነጩ የበላይነትንና የጥሬ ሀብት ዘረፋ የማያመቹ መንግስታትን ማስወገድና በነሱ አፈ ቀላጤዎች ተተክቶ ህብረተሰብአዊ ውዝግብን መፍጠር ነው። በዚያውም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች በምንም ዐይነት የሳይንስና የቴክኖሎጂ ባለቤት ሆነው ስነ ስርዓት ያለው ህብረተሰብ እንዳይመሰርቱ ነው። የዛሬው በብሬዚደንት ቡሽ የሚወከለው እጅግ አክራሪ በሆኑት በምክትል ፕሬዚደንቱ ቼኒ ፣ ረምስፌልድ ፣ በአሁኑ ወቅት የዓለም ባንክ ፕሬዚደንት

የሆኑት ዎልፎቪትዝና ሌሎች በስቴት ዴፓርትሜንት ውስጥ የተሰገሰጉት የኒዎ ፋሽሺስት ኃይሎችና የእነዚህ ከኢንዱስትሪ-የሚሊታሪ ኮምፐሌክስ ጋር መቆላለፍ የሚያመለክተው የአሜሪካንን ዲሞክራትነትን ሳይሆን በአሜሪካን የውስጥ ፖለቲካና የህብረተሰብ አወቃቀር እጅግ አደገኛ የሆነ አዲስ ኃይል ብቅ እንዳለ ነው። ለዚህም ነው እነ ቡሽና በዚህ ሲናርክሲስት አወቃቀር የወደቁት የምዕራብ ፖለቲከኞች ከሰኔ ወር ጀምሮ በአገራችን ውስጥ ለሚፈጸመው እልቂት የጆሮ ዳባ የሚሰጡትና የተቃዋሚውን ኃይል በዚህም በዚያም ብለው ለማዳከም ተንኮል የሚሸርቡት።

ያም ሆነ ይህ እነቶ መለስ ስልጣን ከመያዛቸው በፊት በለንደን ላይ ከሌሎች ብሄር-አቀፍ ሳይሆኑ ፣ ነፃ አውጪ ተብዮች ጋር በአሜሪካን እንባ ጠባቂነት ሲሰበሰቡና የአገራችንን የወደፊት ዕጣ ለመወሰን ሲንደፋደፉ ይህ ከላይ የተነተንኩት ዓለም አቀፋዊ የሲናርክሲስት ኃይል ከበስተጀርባቸው እንዳለ በማወቃቸው ነው። በተጨማሪም አሜሪካን ውስጥ ለውስጥ በአደራጃቸው የሲ አይ ኤ ሰዎችና ፕሮ አሜሪካን የሆኑ ፣ የኋላ ኋላ በዩናይትድ ኔሽን ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የተሰጣቸው ወይም የጡረታ አበል እየተከፈላቸው እንዲኖሩ የተደረጉት ኢትዮጵያውያን ኃይሎች ተግባራቸው መንገዱን ለወያኔና ለሻቢያ ማመቻቸት ነበር። ስለሆነም ለንደን ውስጥ በወያኔ ፣ በሻቢያና በኦኤል ኤፍ መሀከል ስምምነት ሲደረስና እዚያው ለንደን ሆነው ሲያቆበቁቡ የነበሩት ቀደም ብለው አንዳንዶቹ በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ በመሪነት ደረጃ የተካፈሉት ርዕዮተ ዓለማቸውን የሸጡ ግለሰቦች ፣ እንድርያስ እሸቴና በአንድ ወቅት የውጭ ኢኮኖሚ ግኑኝነት ተጠሪ የነበረው አብዱል መጂድ አሁን ህይወቱ ያለፈው ፣ የኢትዮጵያን ፊዩዳል ድርጅት በተንኮል ሲያፈራረርስ የከረመውና በፀረ ተራማጅነት ናላው የዞረ  ክፍሌ ወዳጆ እነዚህ ሁሉ ፍርፋሪ ቀማሾች በመሆን የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ለወያኔና ለአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በሚያመች መንገድ ማዘጋጀት ነበረባቸው። በበኩሉም ወያኔ በህብረተሰብአችን ውስጥ አገዛዙን ለማጠንከርም ሆነ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስም ተቀባይነትም ለማግኘት ሲል እነዚህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲፕሎማሲ ልምድ አላቸው የሚባሉ ግለሰቦችን ማሰባሰብ ነበረበት። በዚህም አማካይነት ወደ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጭም ዕርዳታ በማግኘች ኢኮኖሚያዊ መሰረቱን አጠናክሮ አገራችንን ለረጅም ጊዜ እረግጦ ለመግዛት ዕድል አገኘ።

በእነ አቶ ክፍሌ ወዳጆ የተዘጋጀውን አገር አፍራሽ ህገ-መንግስትም ሆነ ተግባራዊ የሆነውን የክልል ፖለቲካና እ. አ በ1993 ዓ.ም በአይ ኤም ኤፍና በዓለም ባንክ የተዘጋጀውንና ተግባራዊ የሆነውን የስትርክቸራል አድጀስትሜንት ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ስንመረምር የምን ደርስበት ድምደማ የወያኔ ህልም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን ለረጅም ጊዜ ለማሸት ዕድል ያገኘው አሜሪካን ህልሙ ተግባራዊ ሊሆን የቻለበት ጊዜ ነው። የክልሉን ፖሊሲ ስንመለከት በጊዜው በኢትዮጵያ የነበረው የአሜሪካን አምባሳደር በኢትዮጵያ ቴሌቪዥ ወጥቶ የኢትዮጵያን ህዝብ ሊያስተምር እንደሞከረው ፣ ፖሊሲው በአፍሪቃ ውስጥ እንደምሳሌነት መወሰድ ያለበት ፕራክቲካል ፖለቲካ ነው ብሎ ነው መዘላበድ የጀመረው። ይሁንና ይህ ዐይነቱ በአሜሪካንና በግብረአበሮቿ የተደገፈው የክልል ፖለቲካ ፀረ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ለአገራችን የኋሊት ጉዞ እንደነበር ፣ ፖለቲካዊ ነፃነትንና ዕውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ባህልን እን ደማያመጣ ግልጽ ነው። አገሮች ከረጅም ጊዜ የህብረ-ብሄር ግንባታ በኋላ ፣ በብዙ የአፍሪቃ አገሮች ባይጠናቀቅም ፣ ያካበቱንን አብሮ የመኖር ባህል አፈራርሶ ትናንሽ መንግስታት አቋቁሞ በራሳችሁ ክልል ተሽከርከሩ ማለት ፀረ-ሳይንስና ፀረ-ዲያሌክቲክ ነው። ምክንያቱም አንድ ነገር ከትንሽ ወደ ከፍተኛው ወይም ወደ ትልቅ መሸጋገር ወይም ማደግ ስላለበት ነው። ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ የሆነው የክልል ፖለቲካ ነፃነትን ሳይሆን ልዩ ዐይነት የክልላዊ ስሜትን ያዳበረ ፣ ፍቅርንና ተከባብሮ አብሮ መኖርን ሳይሆን ጥላቻን ያሳደረ ፣ ህብረተሰብአዊ ኃይል እንዳይጎለምስና ለዕድገት እንዳያመች የተደረገበት ብሄረ-ሰቦችን በነፃነት ስም እዚያው በዚያው ቀጭጨው እንዲቀሩ ያደረገ ኋላ ቀር ፖለቲካ ነው። ለእነ አሜሪካና ለተቀረው የምዕራቡ ዓለም እንደዚህ ዐይነቱ የክልል ፖለቲካ በአገር ውስጥ ገብቶ ለመፈትፈትና አለመረጋጋት እንዲፈጠር ለማድረግ የሚያመች ጥሩ አጋጣሚ ነው። ለዚህም ነው እነ ወያኔ ስልጣን ከጨበጡ በኋላ የነጭ ዘር በኢትዮጵያ ውስጥ መጉረፍ

የጀመረው። ለዚህ ነው ዛሬ ወደ አምስት መቶ የሚጠጉ መንግስት ነክ ያለሆኑ የተራድዖ ድርጅቶች በአገሪቱ ውስጥ እንደ አሳ የሚዋኙት። ለዚህ ነው አገራችን አይታ በማታውቀው መልክ የልዩ ልዩ ሴክቶችና የኢትዮጵያን ክርስትና ሃይማኖትም ሆነ የእስልምናን ሃይማኖት የሚቀናቀኑ ሃይማኖቶች እንደ አሸን ፈልተው ህዝብንና አገር የሚያዋክቡትና ባህልን ለማደፈራረስ ሁኔታዎችን የሚያዘጋጁት። ከዚህም በላይ አዲስ በተፈጠረው የፖለቲካ ሁኔታ ህብረተሰብአዊ ባህል መበላሸት ብቻ ሳይሆን በተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል መሀከል ያለው የርዕዮተ-ዓለም አስተሳሰብ እንዲበወዝ የተደረገበትና ከውጭ በኤክስፐርት ስም የሚመጡት የውጭ ዜጎችም ሆነ ኢትዮጵያውያን ኃይሎች በሚሰጡት ሳይንሳዊ ያልሆነ ትንተና- ለምሳሌ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሂደት ላይ የግሎባል ኢኮኖሚ የሚያደርገው ጫና በጣም ዝቅተኛ ነው ብሎ በጥናት ማቅረብ- የተወሰነውን ኃይል ግራ እንዳጋቡት የታወቀ ነው። ሌሎችም በታወቁ ዓለም አቀፋዊ ኤክስፐርቶች ይሰጥ የነበረው ትንተናና ምክር ፣ ከፍተኛ ዕውቀታቸው ባያጠራጥርም ፣ የአገራችንን የህብረተሰብ አወቃቀር ፣ የአኗኗር ስልትና የኢኮኖሚ ቅንጅት በፍጹም ያላገናዘበ ነው። ስለሆነም ነው የአገሪቱ ኢኮኖሚ የድህነት ኢኮኖሚ ለመሆን የበቃውና ከዐመት ዐመት ኢኮኖሚው እየዘቀጠ የሄደው። አገራችንም በቁልምጫ ስም የለጋሽ ሰጪዎችን እጅ እያየች እንድትኖር የተገደደችው።

ከዚህ ተነስተን እ.አ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ በነፃ ገበያ ስም ተግባራዊ የሆነውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንመለከት በትክክልም የእነ አሜሪካንን ህልምና ፍላጎት ያሟላ ፣ አገራችን ለብዙ ዐመታት በግሎባል ኢኮኖሚ ስር እየዳሸቀች እንድትኖር ፣ በዚያውም የስልጣኔው ዘመን የት እየለሌ ያደረገ ሳይንሰ አልባ ፖሊሲ ነው። ይህ ፀሀፊ በወቅቱ በተከታታይ የዚህን ሳይንሰ አልባ የሆነ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ምንነት በጦቢያ መጽሄትና በዌብ ሳይቶች ላይ አውጥቶ እን ዲነበብ አድርጓል። እንደዚሁም ለአገራቸው የሚቆረቆሩ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ኤክስፐርቶች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል። በአገራችን ተግባራዊ እየሆነ በመምጣት ላይ ያለው የገበያ ኢኮኖሚ ጥቂቶችን የጠቀመና ያጎለመሰና በሌላ በኩል ደግሞ ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነውን ህዝባችንን ወደ ድህነት የገፈተረ ለመሆኑ በጥሩ ብዕራቸው አሳይተውናል።

ይህ እ.አ በ1993 ዓ.ም በአይ ኤም ኤፍና በእነ ዓለም ባንክ የተጠናቀረው የኢኮኖሚክ ፖሊሲ እንደተለመደውና አጅግ ፀረ-ሳይንሳዊ በሆነው የኒዎ-ሊበራል የትንተና ዘዴው የኢትዮጵያን ኢኪኖሚ ካተተ በኋላ የደረሰበት ድምድማ ኢኮኖሚው ከዕዝ/ኮማንድ/ ተላቆ ወደ ነፃ ገበያ መሸጋገር እንዳለበት ነው። በዚህ መንገድ ብቻ ኢኮኖሚው እንደሚያድግና ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብም ብልጽግናን ተጎናጽፎ በደስታ እንደሚደነፍቅ ያበሰርልናል። ለዚህም እንደመፍትሄ ብሎ ያቀረባቸው ፣ 1ኛ) በመንግሰት ቁጥጥር ስር ያሉ ካምፓኒዎችና የንግድ መደብሮች ወደ ግላዊነት ተሸጋግረው በነፃ ገበያ ደንብ መሰረት መተዳደር አለባቸው። 2ኛ) የውጭው ንግድ ሊበራላይዝ መደረግ አለበት። በሌላ አነጋገር ወደ ውስጥ የሚገቡም ሆነ ወደ ውጭ የሚወጡ ዕቃዎች እንደ ቀረጥ ካሉና ሌሎች ታሪፍ ነክ ካልሆነ ማነቀዎች መለቀቅ አለባቸው። 3ኛ) የውጭው ከረንሲ በጊዜው ከነበረው የብር/ዶላር ለውውጥ ከ2.07 ወደ አምስትና ከዚያም ከፍ እያለ በማደግ/ዝቅ በማለት ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምታወጣው ዕቃ የተሻለ የመሸጥ ዕድል ያገኛል። 3ኛ) የመንግስት ድጎማዎች/ሰብዲዚ/ መቀነስና ባጀቱም መስተካከል አለበት። በሌላ አነጋገር ለማህበራዊና ለጤና የሚወጡ ወጪዎች መቀነስ አለባቸው። በእነ አይ ኤም ኤፍ የሞነቴሪ ፖሊሲ ፍልሰፍና ይህ ዐይነቱ የባጀት ቅነሳ የመንገስቱን ባጀት ከማረጋጋት አልፎ ዲይናሚክ ለሆኑ የገበያ ኃይሎች ኤንቬሰት ለማድረግ ዕድል ያገኛሉ። ገንዘብ ከፍጆታ ወደ ምርታማ መስክ በመሸጋገር ለኢኮኖሚው ዕድገት ዐይነተኛ ኃይል ይሆናል። 4ኛ) የውጭውን የንግድ ሚዛን መዛባት ማስተካል። ይህም ለጊዜው በብድር ሲሆን ፣ ከረጅም ጊዜ አንፃር በዴማንድና ሰፐላይ አማካይነት ወደ መስተካከል ያመራል። እነዚህ መሰረታዊ የአይ ኤም ኤፍ ፖሊሲዎች ሲሆኑ በዓለም ባንክ የተጠናቀረው የመዋቅር/ስትራክቸራል አድጀስትሜንት/ፖሊሲ ይህንን የሚያጠናክርና ከኢኮኖሚ አልፎ ወደ ኢንስቲቱሽናላዊ ፣ ማለትም የፊናንስና የባንክ

ሪፎርም የሚያመራ ነው። በእዚህ ዐይነቱ የተሟላ ፖሊሲ ብቻ አገሪቱ ዕውነተኛ ወደ ሆነ ነፃ ገበያ ታመራለች ብሎ ይደመድማል።

እዚህ ላይ ሰፊት ትችትን ከመስጠት ተቆጥቤ ፣ ፖሊሲው ሳይንሳዊ አይደለም የምላቸውን አንዳንድ መሰረታዊ ጉዳዮችን ጠቅሼ ለማለፍ እፈልጋለሁ። በመጀመሪያ የአገራችን ኢኮኖሚ በዕዝ ኢኮኖሚ/ኮማንድ/ ነበር የሚመራው ብሎ ማተት ከመጀመሪያውኑ ስህተት ነው። ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት በአፄ ኃይለስላሴ  ዘመን ዘመናዊ የሚባለው መስክ ምንም ሳይንሳዊ መሰረት የሌለውና ራሱ በነፃ ገበያ ደንብ የሚንቀሳቀስ እንዳልነበር ነው። በጥቂት ኦሊጎሎፖሊሰቶች ይካሄድ የነበረ ፣ በፍጆታ ምርት ላይ ብቻ ያተኮረና ከገጠር ወደ ጥቂት ከተማዎች ሀብትን እየሟጠጠ በመውሰድ ድህነትን ያስፋፋ ነው። ስለሆነም ኢንዱስትሪዎችም ሆነ ሌሎች የኢንሹራንስ ፣ የፊናንስና የባንክ ተቋሞች ሲወረሱ ይህንን ስትራክቻራል ድክመት ለመወጣት እንደነበር አይታበልም። ችግሩ ግን በጊዜው ሶሾሊስታዊ አድልዖ ወይም ደግሞ በዚህ መንገድ ብቻ ኢኮኖሚውን ማሳደግ ይቻላል ተብሎ ስለታመነበት አብዛኛውን ጊዜ ካለመግባባትና በጥርጣሬ ከመመልከት የተነሳ ብዙ ስህተት ተፈጽሟል። ይህ ጉዳይ ግን እ.አ በ1976 ዓ.ም በወጣው የብሄራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም እንዲታረም ቢሆንም በየጊዜው በነበረው የኃይል አሰላለፍ ለውጥና ውዝግብ በፍጹም ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። በብሄራዊ ዲሞክራቲክ ፕሮግራሙ መሰረት ብሄራዊ ከበርቴ ለማዳበር ፣ ኢኮኖሚውን በሰፊ መሰረት ላይ ለመገንባት ነበር። ይህ በፍጹም አልተቻለም። ከዚህም ስንነሳና ብዙዎችም የኢትዮጵያን አብዮት ብሄራዊ ባህርዩን ገንጥለው በጥላቻ ስለተመለከቱትና ፣ በአንድ በኩል እነሱ ባካሄዱት ጦርነትና ውዝግበ ፣ -አወቀውም ሆነ ሳያውቁ- በሌላ ወገን ደግሞ ራሱ በደርግ ውስጥ ያለው የኃይል አሰላለፍ ለውጥና ወዝግብ እንዲሁም መደናበር በጊዜው ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮግራሞችን በስራ ላይ ማዋል አልተቻለም። ይህንን የምንለው በቀና ዐይን ስንመለከተውና በንፁህ ጭንቅላት ስንመረምረው ነው። ከዚህ የተደናበረና በጊዜው አወዛጋቢ ከሆነው የኢትዮጵያ ሁኔታ ተነስተው እነ አይ ኤምፍ የደረሱበት ድምደማና ደርግ እስከ ወደቀበት ጊዜ ድረስ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ፖሊሲ ይካሄድ ስለነበር ፣ አሁን ኢኮኖሚውን በነፃ ገበያ መርሆች ላይ ነው ማዋቀር ይገባል ብለው ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ውጭ የሆነ የካፒታሊሰት የኢኮኖሚ ሎጂክንና ፕርንሲፕልን ያልተከተለ ፖሊሲ ተግባራዊ እንዲሆን ለወያኔ አዘጋጅተው የሰጡት። በሌላ አነጋገር ፣ የአገራችንን የሶሺዮ ኢኮኖሚክ ሁኔታ ያላገናዘበ ፣ የኢኮኖሚውን ውስጣዊ ደካማነት/ስትራክቸራል ዊክነስ/ ያላጤነ የኢኮኖሚክ ፖሊሲ ነው በወያኔ አገዛዝ ተግባራዊ መሆን የጀመረው። የስትራክቸራል ዊክነስ የምለው ፣ በምርት ማመረቻ መሳሪያዎችና የፍጆታ ዕቃን በሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች መሀከል ምንም ዐይነት ውስጣዊ ግኑኝነት/ኦርጋኒክ ሊንክ/ አልነበረም። ኢኮኖሚውም በዚህ መልክ አልተዘጋጀም። በሁለተኛ ደረጃ ፣ ኢትዮጵያ ለውጭ ንግዷ በተወሰኑ የጥሬ ሀብቶች ብቻ ስትመካ እነዚህም በፋብሪካ ተፈብረከው የሚላኩ አልነበሩም። አይደሉምም። ሶስተኛ ፣ ኢንዱስትሪዎችን ፋይናንስ  ማድረግ ያለበት የባንኩ መስክ የበለጠ በከተማዎች የተከማቸና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ሳይሆን ከንግድ መስኩ ጋር ብቻ በመያያዙ በአጠቃላይ ሲታይ ኢኮኖሚው ውስጣዊ ኃይል ማግኘት አልቻለም። ከዚህ ጋር ተያይዘው በየክፍለ ሀገራቱና በየወረዳዎችም ሆነ በመንደር ያሉት ኋላ ቀር ኢንስቲቱሽኖችና መስሪያ ቤቶች ለገበያ ኢኮኖሚ አመቺ ሆነው ባለመደራጀታቸውና በተጨማሪም ደግሞ ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገር የመጣው ከካፒታሊስት ሎጂክ ጋር የማይጓዝና የማይጣጣም የአኗኗርና የአሰራር እንዲሁም የአደረጃጀት ስልት እንቅፋት በመሆኑ እንደተጠበቀው የደርግ ሶሾሊዝምም ሆነ የመጨረሻ መጨረሻ የወጣው የገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም።

ያም ተባለ ይህ ፣ የእነ አይ ኤም ኤፍ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ፀረ-ሳይንስ ነው አይደለም ተባለ ፣የአሜሪካንም ሆነ የእነ አይኤም ኤፍ ዐላማ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሳይንሰና የቴክኖሎጂ መሰረት ሰጥቶ የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲያድግና አገራችን እንደአገር አብባ ህዝባችን ከድህነት እንዲላቀቅ ማድረግ አይደለም። ጆን ፐርኪንስ የተባለው በሰባኛው ዓመተ ምህረት  ለአንድ ትልቅ በሲ አይ ኤ በተተበተበ ካምፓኒ ተቀጥሮ ሲሰራና አሁን እራሱ

በሰራው ወንጀል እራሱን አጋልጦ ጥሩ ስራ ለመስራት እንደተነሳው ነጭ አሜሪካዊ አገላለጽ- ብዙ ነግሮች የታወቁ ናቸው- የአሜሪካንም ሆነ የእነ አይ ኤም ኤፍና ዓለም ባንክ ፖሊሲ የሶስተኛውን ዓለም ኢኮኖሚዎች ማሳደግ ሳይሆን የተሳሳተ ፖሊሲ በመንደፍ የተወሰኑ ኃይሎችን ማበልጸግና ሰፊውን ህዝብ ደግሞ ማድኸየት ነው። እ.አ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ በነፃ ገበያ ስም የተካሄደውም ፖሊሲ ሰፊውን ህዘብ የባሰ ደህና አቅመ ቢስ በአንድ በኩል ያደረገ ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በኢንተርናሽናል የአገዛዝ ሂራርኪ ውስጥ ሊታቀፉ የሚችሉ ኃይሎችን ስልጣን ላይ በማውጣትና የተሳሳተ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ እንዲከተሉ በማስገደድም ሆነ በማሳሳት ዕውነተኛ ህብረተሰብአዊ ሀብት እንዳያብብና የስልጣኔውም ዘመን እን ዲራዘም ፣ በዚያውም እንደኛ ያለው ምስኪኑ ጥቁር ህዝብ እየተተራመሰ እንዲኖር ያደረገ ነው። አስራ አራት ዓመት ያህል በአገራችን ጎልቶ የሚታየው ሀቅ ይህ ነው። ሰሞኑን የሚወጡት ብዙ ትንተናዎች እንደሚያረጋግጡት በአለፉት አስራ አራት ዓመት አሜሪካን ብቻ ለወያኔ መንግሰት "በዕርዳታ" መልክ $ 21 ቢሊዮን የሚጠጋ ሰጥቷል። ባጀቱን ለመደጎም ደግሞ በየዓመቱ ከ$1.9 ቢሊዮን በላይ በዕርዳታ መልክ ይሰጣል። ይህ አሜሪካን ለወያኔ የሰጠው ዕርዳታ ፣ የአፄ ኃይለስላሴ መንግስት እ.አ እስከ 1969 ዓ.ም ድረስ ካገኘው ዕርዳታ ጋር ሲወዳደር በ97 እጅ ሲበልጥ ፣ ይህም በአሀዝ ሲተመን በዚያን ጊዜው የዶላር ዋጋ $216 ሚሊዮን ብቻ ነው።

ይህ የእከክልኝ ልከክለህ ፖለቲካና ዕርዳታ ከላይ ለመተንተን እንደሞከርኩት ዝም ብሎ የመጣ አይደለም። የራሱ የሆነ ሎጂክና ታሪካዊ ክስተቶችም እንዳሉት በአጭሩም ቢሆን ተቀምጧል። እዚህ ላይ በጭንቅላት መቋጠር ያለበት ይህ የወያኔን አገዛዝ በዓለም አቀፍ አገዛዝ ሂራርኪ ውስጥ መግባት እነ ምዕራብ ጀርመን በሰማኒያኛው ዓመት የአፍሪቃን መን ግሰታት በቁጥጥራቸው ስር ለማምጣት ካወጡት ስትራቴጂ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። በድሮው ስትራቴጂ ስልት የምዕራብ መንግሰታት ፕሮጀክቶችን ለመርዳት ነበር ልገሳ የሚያደርጉት። በእነሱ ግምገማ መሰረት አርባ ዓመት ያህል የምዕራቡ ዕርዳታ በአፍሪቃ ውስጥ ምንም ለውጥ አለማጠም። ስለሆነም መንግሰታቱን እንደ ፕሮጄክት በመውሰድና ሰርጎ በመግባት ለውጥ ማምጣት ነው የሚል ነው የደረሱበት ድምዳሜ። ሌላ የኒዎ ኮሎኒያል ፖሊሲ ስትራቴጂ ነው ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ነው በወያኔ አገዛዝ ስር በትምህርት ስርዓት አወጣጥ ፣ አስተዳደርን ማስተካከል በሚልና በባንኩ የበለጠ የርዕዮተ ዓለም ተጽዕኖ እንዲኖረው የኒዎ ሊበራል ርዕዮተ ዓለምን በማስፋፋትና በነጮች ቁጥጥር ስር እንዲወድቅ በማድረግ መንግስትም ሆነ ሌሎች ከመንግሰት ጋር የተያያዙ ኢኑስቲቱሽኖች የበለጠ በኒዎ ኮሎኒያል መዳፍ ስር ወድቀው የሚታሹት። ከዚህ ውጪ ፣ የውጭ አገር ካምፓኒዎች በተለይም ምርታማ ያልሆኑና የአገሪቱን ኢኮኖሚ ሊያሳድግና የስራ መስክ ሊከፍቱ በማይችሉ ፣ በመሰረቱ የባርነት ደሞዝ እየተከፈለባቸው የተቋቋሙት እርሻዎች የሚያረጋግጡት የአገራችንን የዕድገት አቅጣጫ የሚያሳስቱት ናቸው። ለእርሻ ምርት ሊያገለግሉ የሚችሉ ፍሬያማ መሬቶችን አበባ መትከያ ማድረግና በሌሎች አልባሌ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር ያልተያያዙ መስኮች ላይ መረባረብ የሚያረጋግጡት ኢትዮጵያ ልዩ ዐይነት የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ የሚካሄድባት አገር እንደሆነች ነው። በአዲስ አበባ ከተማም ለዲፕሎማቶች መኖሪያ እያሉ ደሀውን ህዝባችንን እያፈናቀሉ ፈረንጆች በአንድ አካባቢ ተሰግሰግው እንዲኖሩ እየተከለለ ቪላ ቤት የሚሰራበት ሰፋፊ መሬት የሚያረጋግጠው የቱን ያህል የውጭ ኃይሎች ሚና እየጎለመሰ እንደመጣና በህብረተሰብአችን ላይ የዝቅተኝነት ሰሜት እንዲያድር አገዛዙ የሚጫወተው ሚና ቀላል አለመሆኑን ነው። የዛሬውን የወያኔ አገዛዝ ቀደም ካሉት ሁለት አገዛዞች የሚለየው ይህ ለነጮች ሽር ጉድ ማለቱና ኢትዮጵያ ዕርቃኗን ከፍታ እንድትሰጥ ማድረጉ ነው። በተለይም የመስከረም 11 የቴሮሪሰቶች ድርጊት በአሜሪካንና በወያኔ መሀከል የበለጠ መቆላለፍን ፣ ቴሮሪስቶችን አድናለሁ በሚል በወያኔ አሸርጋጅነት አሜሪካ አገራችንን የማሰስ ዕድል እንዳገኘ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ሰሞኑን በዌብ ሳይት እንዳየነው የአሜሪካን ወታደሮች የወያኔን ጨፍጫፊ ኃይል የመሳሪያ አፈታትና አነጣጥሮ መተኮስ እያስተማሯቸው እንደሆነ ነው። ለወያኔ የተሰጠው ልዩ ብረት ለበስ የወታደር መኪናና መሳሪያ ቴሮሪስቶችን ለመዋጋት እንደሆነ አሜሪካ ለማስረዳት ሲን ደፋደፍ ፣ ይህንኑ አንዳንድ ኢትዮጵያውን ኃይሎችም ሲያስተጋቡና አሜሪካንን ከደሙህ ን

ጹህ ለማድረግ ሲጣጣሩ ተሰምቷል። ይህ የዋህነት ወይም ደግሞ የአሜሪካንን የፖለቲካ ስትራቴጂ ካለማወቅ የሚስተጋባ ወሬ ለብሄራዊ ነፃነትና ለስልጣኔ ለምናደርገው ትግል ትልቅ እንቅፋት መሆኑ መታወቅ አለበት። በአንዳንድ ሁኔታዎች ይህንን የአሜሪካንና የተቀሩ የምዕራብ አገሮች በአገራችን ውስጥ ጣልቃ ገብነትና ከፋፋይነት ለውይይት ቀርቦ ሲወሳ አን ዳንዶች ይህንን እንደማያምኑና እንደማይቀበሉ ሃሳብ ሲሰነዝሩ ተሰምቷል። የፖለቲካ  ትንተና ሳይንስ እንደመሆኑ መጠን በዕምነትና ባለመቀበል ላይ የተመረኮዘ ሳይሆን የተወሰነ ስልትን ተከትሎና ኢንፎርሜሽኖችን ሰብስቦ የሚደረግ ውይይትና ትንተና እንደመሆኑ መጠን እን ደዚህ ዐይነቱ አገርን የሚመለከት ጉዳይ ወዲያውን አልቀበልም ወይም አላምንም በሚለው ኢ-ሳይንሳዊ አባባል መዘጋት የለበትም። ስለዚህም የወያኔን አገዛዝ ጥለን የተከበረችና ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን ለመገንባት በምናደርገው ትግል ውስጥ የውጭ ኃይሎችም ሚና በደንብ መጠናትና ለትንተና መቅረብ አለበት። ካለበለዚያ "አደባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" እንደሚባለው አነጋገር ይሆናል ማለት ነው።

ከዚህ አጭር ትንተና ስነነሳ የግንቦት ስምንቱ ምርጫና ውጤት ለአሜሪካንም ሆነ ለተቀረው የምዕራብ መንግስታት ዱብ ዳ ነው የሆነባቸው። የወያኔ አገዛዝ ለረጅም ጊዜ ይቆያል ብለው የገመቱትና ሳያስቡት የመጣባቸው ህዝባዊ ውሳኔ እስከዛሬ አቅፎ ደግፎ ጌታዬ የሚላቸው ኃይል ከሄደ እንደፈለጉ ሊያሽከረክሩት የሚችሉት ሌላ ኃይል አይኖርም  ማለት ነው። ስለሆነም እንደምንም ብለው ወያኔ የሚቆይበትን መንገድ ፣ ካለዚያም ደግሞ ህዝባዊ ትርምስ እንዲመጣ የማያደርጉት እርኩስ ደርጊት አይኖርም። እንደዚያ በሰኔ ወር የተካሄደው ጭፍጨ እያለ ምንም እንዳልተደረገ በምዕራቡ የዜና ማሰራጫዎች እንኳ በበቂው ማስተጋባት አልፈለጉም። ያነጋገርናቸው ባለስልጣናትም ነገሩን እንዳልሰሙ ፣ ሌሎች ደግሞ በቅንጅት አነሳሽነት የተፈጸመ አድርገው ለማቅረብ ሲንደፋደፉ ተሰምቷል። ለምሳሌ ሴን ሜኮርማክ የሚባለው የስቴት ዴፓርትሜንት ቃል አቀባይ ለተኩሱ መንስኤ ቅንጅት ተጠያቂ መሆንኑ ሲናገር ፣ በአዲስ አበባ አንድ የጀርመን ኤምባሲ ሰራተኛ ተደውሎለት ለምን ዝም ብለው እንደሚመለከቱ ሲጠየቅ ወታደሮቹ ሲተኮስባቸው ታዲያ ምን ያድርጉ ብሎ ነው ከዕውነት የራቀ መልስ የሰጠው። ከዚህ የምንረዳው እነዚህ ምዕራባውያን የቱን ያህል እን ደናቁንና ለዚህም ደግሞ እነ አቶ መለስ ብቻ ሳይሆን በአለፉት ሃምሳ ዐመታት በአገራችን ምድር የተካሄደው ቀደም ብዬ የተነተንኩት ሁኔታ ለአገራችን ክብር መደፈር የበኩሉን አስተዋፅዎ እንዳደረገ ነው። ያም ሆነ ይህ አሜሪካንም ሆነ ሌሎች የምዕራብ መንግሰታት የወያኔ አገዛዝ እንዲወድቅ በፍጹም አይፈልጉም። ለዚህ ደግሞ በአንድ በኩል የመንግስቱን የጭፍጨፋና የጭቆና አገዛዝ ለማጠናክር ከአሜሪካንና ከእንግሊዝ ለወያኔ የተሰጠው የሚሊቴሪ መሳሪያዎች ርዳታ ፣ እነሱ እንደሚሉት ረባሾችን/ቴሮሪስቶችን/ ለመዋጋት ሳይሆን ህዝባዊ ብጥብጥ ቢነሳ ለመጨፍጨፍ ነው። የሰሞኑን የጠቅላይ ሚኒስተር ብሌዬር የአቶ መለሰ የጡት አባት የሆኑት ገለጣ ፣ የአውሮፓ ዩኒየን አንድ በአፍሪቃ ውስጥ ረብሻን ፀጥ የሚያደርግ ኃይል ማዘጋጀት ያስፈልጋል ያሉትም ከዚህ የእነ አቶ መለስን ስልጣን ላይ ለማቆየት ካለቸው ግምትና ዕምነት የመነጨ ነው። በተጨማሪም በሳቸው አዘጋጅነት ከሁለት ሳምንት በፊት የአውሮፓን ኒዎ ኮንሰርቫቲቮችን ጠርቶ አዲስ ዐይነት የፖለቲካ አወቃቀር ለማዘጋጀት መሯሯጥ ከዚህ በየጊዜው ከሚቀያየረው የዓለም ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በተለይም በሶስተኛው ዓለም ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ነው። በተጨማሪም የቴሮሪስቶችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በሚል በጅቡቲ የሰፈረው ኢንዲዩሪግ ፍሪደም የሚባለው የኔቶ ጦር ተግባሩ በዚያ አካባቢ ሊነሱ የሚችሉ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠርና አምባገነኖችን ለማጠናከር እንደሆነ ግልጽ ነው። ከዚህም በላይ በጅቡቲ የሰፈረው ይህ ረባሾችን እቆጣጠራለሁ ባይ የኔቶ ጦር የአገራችንን አንድነት የሚቀናቀኑ የብሄረ-ሰብ ነፃ አውጭ ነን ባይ ድርጅቶችን እንደሚያስታጥቁ ይታወቃል። በአካባቢው እጅግ የተወሳሰበ ሁኔታ እንዳለና የወያኔ አገዛዝ በሚያካሂደው የተተራመሰ ፖለቲካ የአካባቢውን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመከታተል እጅግ አዳጋች እየሆነ መጥቷል።

የአሜሪካንንም ሆነም የምዕራቡን ፖለቲካ በሚመለከት አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ያለው አመለካከት እጅግ አወዛጋቢ ነው። ከተሳሳተ ፓራዳይም በመነሳት አሜሪካን በዓለም አቀፍ

EthioLion.com

ደረጃ ነፃነትንና ዲሞክራሲን እንደሚያግዝና እንደሚያስፋፋ ተደርጎ ነው የሚወሰደው።ዛሬ አፍን ሞልቶ መናገር እንደሚቻለው ፣ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የዓለምን ፖለቲካና የሰውን ልጅ በተሳሳተ መልክ ነው የሚረዳው። ነገሮች ሁሉ በራሳቸው ቆመው ነው የሚታዩትና የሚተነተኑት። በተጨማሪም ዓለም ውስጥ የሚካሄዱት ፖለቲካዎች ሁሉ በተናጠል ነው ግን ዛቤ ውስጥ ተቀምጠው በትንተና መልክ የሚቀርቡት። ከዚህም ስንነሳ ሀይቲ ውስጥ ፣ ኤልሳልባዶር ውስጥ ፣ ኒኳራጉዋ ውስጥ ፣ ኮንጎ ውስጥና በሌሎች የአፍሪቃና የላቲን አገሮች በአሜሪካንና በተቀረው የምዕራቡ ዓለም የሚካሄዱት የውክልና ጦርነቶች እኛን የሚመለከቱ አይደሉም። በአጭሩ የምዕራቡ ዓለም በተለይም አሜሪካን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያኖችን ከልቡ ስለሚያፈቅራቸው አገራችን እንድትፈራርስ አይፈልግም። ይህ ዐይነቱ በማንኛውም የፖለቲካ ፍለስፍናና ሳይንስ ያልተደገፈ አስተሳሰብ ጭንቅላታችንን እስከቆለፈው ድረስ የኢትዮጵያን ነፃነት አዲዮስ ማለት አለብን።

በሰፊው ለማሳየት እንደሞከርኩት ፣ በህብረ-በሄር/ኔሽን ስቴት/ ምስረታ ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ቢያንስ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተካሄዱት ትግሎች የሚያረጋግጡት የበላይነትን /ዶሚናንት/ ለማስፈን ነው። እንግሊዝ በኢንዱስትሪ አብዮት መጥቃ ስትሄድ ሌሎች የአውሮፓ አገሮች በእርሻ ምርት ላይ እንዲያተኩሩና በእዚያው ቀጭጨው እንዲቀሩ የማትሸርበው ተንኮል አልነበረም። በከፍተኛ የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ ትግል በተለይ እንደ ጀርመን ያሉት ራሳቸውን ነፃ ማውጣት ችለዋል። የአሜሪካን አሰራሶስት የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች በስንት ትግል ነው ነፃ የወጡት። ነፃ ከወጡም በኋላ አሜረካ የማኑፋክቱር አብዮት እንዳታካሂድ እንግሊዝ የውስጥ አርበኞችን እያደራጀች የማትሸርበው ተንኮል አልነበረም። በእነ አብራሀም ሊንክን ፣ በእነ ሀሚልተን ቆርጥነትና ብልህነት ነው አሜሪካን በአጭር ጊዜ ውስጥ ድልን ተቀዳጅታ የሳይንስና የቴክኖሎጂን ፈር መከተል የጀመረቺው። ይሁንና ይህ አነሳስና ሂደት ውስጥ ባለው ያልሰከነ ኃይል አሰላለፍ ለጠቅላለው ህዝብ ሙሉ ነፃነትን አላመጣም። በተለይም ጥቁሩ አሜሪካዊ ኮፖለቲካም ሆነ ከኢኮኖሚ ሄደትና ሀብት እን ዲገለል በማድርግ እሰከ ዛሬ ድረስ የነጭ የበላይነት ሰፍኖና ጥቁሩ ደግሞ የዝቅተኛ ስሜት አፍኖት የሚኖር ሆኗል።

ዛሬ የምናየው ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ውዝግብና የኢኮኖሚ ዕድገት መዛባትና በሀብታምና በደሀ መሀከል ያለው ልዩነት አንዳንዶቹ ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት ተፈጥሮአዊ አይደለም። ወይም ጥቂቱ የነጭ ዘር ልዩ ተፈጥሮአዊ የማሰብ ኃይል ስላለው አይደለም። በዓለም አቀፍ ደረጃ ፣ በተለይም ከሁለተኛው  ዓለም ጦርነት በኋላ የተስፋፋው ርዕዮ ዓለምና የነፃ ገበያ አስተሳሰብ ብዙዎቻችንን ስላቀፈው የዕድገቱ ፈለግ እንዲጠፋ ተገዷል። ጠጋ ብሎ ለተመለከተው ግን በነፃ ገበያ ሽፋን ስር የሚካሄደው ትግል የበላይነትን ለማሰፍንና ዕውነተኛ ህብረ-ብሄር እንዳይመሰረት ነው። ከ1950ዎቹ ጀምሮ በሶስተኛው ዓለምና በኢንዱስትሪ አገሮች የተካሄዱት የተዛቡ የንግድ ልውውጦች/ አን ኢኳል ኤክስቼንጅ ትሬድ/ ፣ የሶስተኛው  ዐለም አገሮች አሁንም በአማዛኙ የጥሬ ሀብት አምራች አገሮች ሆነው መቅረት ፣ በተለይም እ.አ ከ1973/74 ጀምሮ በዕዳ ወጥመድ መተብተብና የወለድ-ወለድ ከፋይ ሆኖ ለብዙ ዐመታት መቆየት ፣ በተለያዩ ዘዴዎች ከውስጥ ወደ ውጭ ሀብት እን ዲፈስ ማድረግና ወደ ውስጥ ደግሞ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ግንባታ እንዳይካሄድ እንቅፋት መፍጠር ፣ በሊበራላይዜሽን ስም ከውጭ ዕቃዎች እየመጡ የአገር ገበያ መውረርና ከውስጥ የማምረት ኃይል እንዲዳከም ማድረግና የውስጥ ገባያ እንዳይዳብር ማገድ ... ወዘተ ፣ እነዚህ ሁሉ የሚያረጋግጡት ይህ ዓለም አቀፋዊ እየተባለ በቁልምጫ የሚጠራው የካፒታሊስት ኃይል የኛን ዘለዐለማዊ  ባርነት እንጂ ነፃነት እንደማይሻ ነው። ሺህ በሺህ የሚቆጠሩ ጥናቶችም ይህንን ነው የሚያረጋግጡት። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚን ቀሳቀሱት ኢንስቲቱሽኖችም ተግባራቸው ይህንን በሂራርኪ የተዋቀረ ዓለም ማጠናከርና እን ዳይፈራርስ መከላከል ነው። ዛሬ የግሎባላይዜሽን ዘመን ነው ተባለ አልተባለ ሁኔታውን የሚለውጠው አንዳችም ነገር የለም። በዚህ ሽፋንና በነፃ ንግድ ጥላ ስረት የሚካሄዱት ፖለቲካዎችና ፖሊሲዎች በሙሉ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዳይስፋፉ

ለማድረግ ነው። የዓለምን ፖለቲካ ከዚህ ውጭ ለመረዳት መሞከር አደገኛ ብቻ ሳይሆን የዋህነትም ጭምር ነው።

## የግንቦት ስምንቱ ምርጫ የፈጠረው አዲስ ሁኔታ

የወያኔ አገዛዝ የግንቦት ስምንቱ ምርጫ እንዲካሄድ ሁኔታውን ሲያመቻች በህዝባዊ ምርጫ ለሌላ አምስት ዐመት ተቀበያነትን /ሌጂሚቴሲ/ ለማረጋገጥና አማራጭ ኃይል የሌለው መሆኑን ለማሳመን ነበር። በዚህም ወደ ውጭ ተቀባይነትን አግኝቶ በከፋፍለህ ግዛው ፖለቲካው የኢትዮጵያን ህዝቦች የሰቆቃ ዘመን ለማራዘምና የስልጣኔ ጥማታቸውን ለማጨለም ነው። በተጨማሪም ብሄራዊ ነፃነታችንን የበለጠ በማስደፈር የህዝባችንን አቅመቢሰነት ለማሳየትና ጥገኝነትን ለማረጋገጥ ነው።

ከዚህ ቀደም ባወጣኋቸው ጽሁፎች ለማሳየት እንደሞከርኩት ፣ ከምርጫው በፊት የተካሄዱት ውይይቶች ፣ ከምርጫው አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ የተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍና እንዲሁም የሰፊው ህዝብ የምርጫ ተሳትፎና ውጤቱ የአገራችንን የፖለቲካ ሁኔታና የኃይል አሰላለፍ መሉ በሙሉ እንደቀየረው ነው። የምርጫው ውጤት መጭበርበርና የህዝባችን ተቃውሞና የሰኔው ጭፍን ጭፍጨፋ የወያኔን ዕውነተኛ ባህርይ ፣ ተቀባይነት ማጣትና በሌላ ወገን ደግሞ የህዝባችንን አንድነትና ለዲሞክራሲና ለዕድገት ያለውን ፍላጉት በጉልህ ያረጋገጠበት ሁኔታ ነው። የምርጫው ውጤት አለመታወቅ እየተራዘመ በሄደ ቁጥር ፣ በህዝቡ ዘንድ ያለው ቁጣ እየፋመ መሄድና አገዛዙም ይህንን ህዝባዊ ቁጣ ለማብረድ በሰላም ሳይሆን በግልጽና ውስጥ ለውስጥ በሚወስዳቸው የጭቆና እርምጃዎች የባሰውኑ እየተጠላ የመጣበትና በቀላሉ ሊወጣ የማይችለው አጣብቂኝ ውስጥ የገባበት ሁኔታ እንደሆነ መመልከት ችለናል። እንደገና የህዳሩ ጭፍጨፋ ፣ ህዝቡ የመረጣቸውን የቅንጅት መሪዎች በሀሰት ወንጅሎ እስር ቤት ውስጥ ማጎር ፣ ደጋፊውን ህዝብ ማሰቃየትና በተለይም ወጣቱን እየተከታተለ መግደልና ማሰር አዳዲስ ሁኔታዎችን እየፈጠረና ፣ በአንድ በኩል ራሱ አገዛዙ ከፖለቲካ ብልህነት ይልቅ እልከኝነትን የመረጠበት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በህዝብ የባሰውኑ እንዲጠላና እንዲናቅ ፣ "ልታስተዳድረን አትችልም" እየተባለ የሚፌዝበት አገዛዝ ነው። ይሁንና ይህ እንደዚህ እንዳለ ከህዝቡ ውሳኔ ይልቅ ራሱ የወያኔ ተመራጮች የሚያሾፉበት ፓርላሜንት ውስጥ ገብተን እንታገላለን ባሉት እነ ዶክትር መራራ ጉዲና ፣ ዶክትር በየነ ጴጥሮስና አሁን ደግሞ በአቶ ልደቱና ተከታዮቻቸው የተማመነው የእነ አቶ መለስ/ሰመኡን በረከት የተቃዋሚውን ኃይል የሚያዳክምና የህዝቡን ቁጣ ማብረድ የሚችል መስሎት ነበር። በዚህ የህዝብን ተወካዮች የማዳከምና የመበታተን ሴራ እንደተከታተልነው አሜሪካን ፣ እን ግሊዝና ጀርመን በግንባር ቀደምትነት አስፈላጊውን የስለላና ህዝብን የመጨፍጨፊያ መሳሪያ ለአገዛዙ እንዳቀረቡለትና እንደሚያቀርቡለት ግልጽ ነው። ይህ ሁሉ ሆኖ ህዝቡ ይበልጥ እየተሳሰረና በቅንጅት መሪዎችም ላይ ያለው ዕምነት ከቀን ወደ ቀን እየጎላ በመምጣት ማን ም ሳይመራው ህይወቱን በመሰዋት ትግሉን በማጧጧፍ ላይ ይገኛል። በአጭሩ የግንቦቱ ስምንት ምርጫና መጭበርበር ፣ የቅንጅት አመራር ቆራጥ ትግልና የህዝባችን ያልተቋረጠ ድጋፍና ትግል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የአንዳንድ ግለሰቦች ክህደትና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከወያኔ ጎን መቆም ማን ለምን እንደሚታገልና የቱን ያህልስ ዘልቆ መሄድ እንደሚችል ቁልጭ አድርጎ የሚታይበት የፖለቲካ ሁኔታ በአገራችን ተከስቷል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ንቃተ ህሊናና ቆራጥነት እንዲሁም እጅ ለእጅ መተሳሰር ለፖለቲካው ሁኔ ታ ልዩ እምርታ ሰጥቶታል። የወያኔ አገዛዝና ከህዲዎች እንዲሁም ትግሉን ለማዳፋን የሚሯሯጡ የውጭ ኃይሎች በቀላሉ ሊገቱትና ሊቆጣጠሩት የማይችሉት ሁኔታ ተፈጥሯል ማለት ይቻላል።

ይህ አንደኛው የግንቦቱ ምርጫ የፈጠረው አዲስ የፖለቲካ ሁኔታ ሲሆን ፣ አገዛዙ የቀን ተቀን በሚወስደው ጭፍን ፖለቲካ በምርጫው ያልተካፈሉ ብሄራዊ ባህርይ አለን የሚሉ

ኃይሎችና ለብሄረ-ሰብአችን መብት እንታገላለን የሚሉ  በሰሜንም ሆነ በደቡቡ የኢትዮጵያ ግዛት እየተጠናከሩ በመምጣት ላይ ናቸው። ይህ ልዩ የፖለቲካ ክስተት ለአገዛዙ ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው የአገራችን ደህንነትና የፖለቲካ ዕድገት አሰቸጋሪ ሁኔታ እንደፈጠረና እን ደሚፈጥር የማይታበል ሀቅ ነው። ወያኔ አስቦም ሆነ ሳያስብ የህዝቡን ምርጫ አዳፍናለሁ በሚል ሌላ በቀላሉ ሊወጣ የማይችለው አዲስ ሁኔታ እንዲፈጠር አደረገ። "የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች" እንደሚሉት አነጋገር ነው። ያም ሆነ ይህ የእነዚህ እያበጡ የመጡ ኃይሎች የፖለቲካ አጀንዳ ምን እንደሆንና ርዕያቸውስ ምን እንደሚመስል ፣ ከዚህ በላይ ደግሞ የተወሳሰበውን የአገራችንን የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊ ችግርና አገርን የመገንባት ጉዳይ በምን መልክ እንደሚፈቱትና እንደሚወጡት ካለነሱ በቀር በግልጽ ማንም የሚያውቅ የለም። የዛሬው የወያኔ አገዛዝ ስልጣኑን ቢለቅ ወይም ከስልጣኑ ቢወገድ የግንቦት ስምንቱን የምርጫ ውጤት ይቀበሉ አይቀበሉ ፣ ለፖለቲካና ወደፊት ለሚነደፈው አዲስ ህገ-መንግስት ይገዙ አይገዙ ፣ ባጭሩ ሰላማዊና ዲሞክራሲዊ የፖለቲካ ሂደትን ይቀበሉ አይቀበሉ ካሁኑ መናገር በጣም አስቸጋሪ ነው። ህዝባችንም ሆነ ተመራጮቻቸው ሌላ ፈተና ይኖርባቸዋል ማለት ነው።

ይህ አዲስ ሁኔታ በእንደዚህ እንዳለ የግንቦቱ ስምንት ምርጫ ለሁሉም ኃይሎች አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ፣ ዲሞክራሲያዊ መርሆችን ተከትሎና ጠብቆ በመከባበር በአገራችን አዲስ የፖለቲካ ባህል ለማካሄድ የሚቻልበት ሆኔታ እንዲፈጠር በር የከፈተ ነበር። በወያኔም ሆነ ከሱ በፊት በነበረው አገዛዝ የተሰሩ ስህተቶችን እንደሰህተት ብቻ በመቁጠርና ይቅር በመባባል በቀና መንፈስ በፕርንሲፕል የተመሰረተ ልዩ የፖለቲካ ባህል በማዳበር የአገራችንን የተወሳሰብ ችግር በጋራ ለመፍታት መወያየትና ለዚህ የሚበጅ ሁሉንም የሚያካትት ህገ-መን ግስት በመንደፍ ወይም ደግሞ ያለውን በማሻሻል ወደፊት አብሮ መጓዝ ይቻል ነበር። የወያኔ መሪዎችም የያዙትን ሀብት ይዘው ህግና ስርዓትን ተከትለው እንደማንኛውም ዜጋ ህይወታቸውን መምራት በቻሉ ነበር። እንደዚህ ዐይነቱ ቀና አስተሳሰብ በቀጥታ በቅንጅት መሪዎች ባይመጣ እንኳ ባላቸው ኃይል ሁኔታው ለነሱ እንዲመቻች ማድረግ በቻሉ ነበር። "ስልጣንን ታግለን ይዘናልና እናንተም ታጥቃችሁ ተዋጉና እዚህ ድረሱ" በሚል ኋላ ቀር ፈሊጥ እልክ ዋስጥ በመግባት አገርን ማተረማመስ ተያያዙ። በዚህ ግትር ባህርያቸው የአገራችንን ሁኔታ የባሰውኑ አሰቻጋሪ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ከእንግዲህ ወዲህ ከነሱ ጋር ምንም ዐይነት የድርድር ሁኔታ እንዳይፈጠር አበላሽተዋል። አገዛዛቸው ብቻ ሳይሆን ህገ-መንግሰታቸውም ተቀባይነት በፍጹም የለውም ማለት ነው። እስከዛሬ ድረስ በፈጸሙት ፣ ማለትም አገርን በማፈራረስ ፣ ብሄራዊ ነፃነትን በማስደፈር ፣ ከውጭ ኃይል ጋር ተባብሮ ቴሮሪዝንም እዋጋለሁ በሚለው ኃይል በቀጥታ አገራችን የቴሮሪስቶች ጥቃት እንዲደርስባት ሁኔታውን ማመቻቸት ፣  የአገራችንን ህልውና ማስደፈርና በሌሎች የጎረቤት አገሮች እን ድትንጠላ ማድረግ ፣ ህዝብን መግደልና ያላግባብ ማሰር ፣ አንዱ ጎሳ በሌላው ጎሳ ላይ እን የነሳ ቅስቀሳ ማድረግና የዘለዓለም ጥላቻ ሰፍኖ መረጋጋት እንዳይፈጠር ሁኔታውን ማመቻቸት ፣ ሀብትን ከአለ አግባብ ማካበትና ሌላው በአገሩ ሰርቶ እንዳያድር የውስጥ ለውስጥ ሴራ መስራትና የአገሪቱ ሀብት እንዲባክን ማድረግ ... ወዘተ. ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ ይሆናሉ ማለት ነው። ባጭሩ ከእንግዲህ ወዲያ በኢትዮጵያ ህዝቦችና በወያኔ መሀከል ምን ም ዐይነት እርቅ አይኖርም ማለት ነው።

## የኛ የትግል ስልትና የአገራችን የወደፊት ዕጣ

በጽሁፉ መግቢያ ላይ እንዳልኩት የተማሪው እንቅስቃሴ ትግሉን ሲጀምር ከአንዳንድ ስህተቶች ባሻገር ይዞ የተነሳቸው የትግል መመሪያዎች ነበሩት። የግንቦት ስምንቱ ምርጫ በአገራችን ታሪክ ውስጥ ልዩ ሁኔታ ቢፈጥርም እኛ እንደተመኘነውና እንደፈለግነው ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። እስካሁን ምርጫ በተደረገባቸው የብዙ አፍሪቃ አገሮች እንደምናየው ፣ የምርጫ ሂደት አዲስ ዲሞክራሲያዊ ባህል ቢሆንም ምርጫ በተካሄደባቸው አገሮች ህዝቦቻቸው ተጠቃሚ ሲሆኑ አይታይም። ለውድድር በሚቀርቡትና በአሸናፊነት በሚወጡት

ፓርቲዎች መሀከል ከመጀመሪያውኑ አገርን የማስተዳደር ፣ ኢኮኖሚውን የማሳደግና ህዝብን ተጠቃሚ የማድረግ አጀንዳ ከመጀመሪያውኑ ግልጽ ባለመሆኑ ስልጣን ከጨበጡ በኋላ መርበትበትና ወደ መባለግ ያመራሉ። በተጨማሪም የእነ አይ ኤም ኤፍንና የዓለም ባንክን ምክርና ፖሊሲ በመከተል ኢኮኖሚያቸውን የባሰውኑ ያተረማምሳሉ። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የናይጄሪያና የኬኒያ ምርጫና ውጤቱ ነው። ሁለቱም አገሮች በአሁኑ ወቅት ምን ዐይነት ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ እናውቃለን።

ወደ አገራችን ስንመጣ ሁኔታው ከዚህ ትንሽ ለየት ቢልም ቀደም ብለው በውይይት ያልተመለሱ አገርን የመገንባት ጉዳይ ተንጠልጥለው ያሉ ናቸው። በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ግንባታ ፣ ከተማዎችን የመገንባት ጉዳይ ፣ ለሰፊው ህዝብ አዲስ የአኗኗርና የአሰራር ባህል መፍጠር ፣ የትምህርቱን ጉዳይ ለሳይንስና ለቴክኖሎጂ እንዲያመች አድርጎ በአዲስ መልክ የማዘጋጀት ሁኔታ ፣ ብሄራዊ ነፃነትን የማስከበር ጉዳይ ፣ ባጭሩ አዲስ ኢትዮጵያን የመፍጠር ጉዳይ። እንደሚታወቀው በሊበራሊዝምና በነፃ ገበያ ስም ብቻ የአገራችንን የተወሳሰበ ችግር መፍታት አይቻልም። ይህንን መርሆ በማድረግ በሰማኒያኛው ዓ.ም ይዘው የተጓዙ ከሚሊታሪ አምባገነንነት የተላቀቁ እንደ አርጀንቲና የመሳሰሉ አገሮች ዛሬ ያሉበትን ሁኔታ ሁላችንም እናውቃለን። ከዚህ ስንነሳ ነፃ ገበያና ሊበራሊዝም የላይ የላዩን ስንመለከታቸው ሁላችንም የምንቀበላቸው ቢሆንም በመሰረቱ የአንድ አገር ህዝብ ኑሮ ካልተሻሻለና አገር መገንባት እስካልተቻለ ድረስ ፅንሰ-ሃሰቦች ቀፎ ብቻ ናቸው ማለት ነው። ስለዚህም የነገሮችን ትርጉም ጠለቅ ብለን እንድንመረምር እንገደዳለን ማለት ነው። በነፃ ገበያ መርሆ እንዴት አንድን አገር መገንባት እንችላለን ? ሊበራሊዝምስ ስንል ምን ማለታችን ነው ? የሚሉትን ጥያቄዎች እንድንመልስ እንገደዳለን። አንድ ቦታ ላይ እን ዳልኩት የአንድ አገዛዝ ምንነት የሚታወቀው መፈክር በማውረዱ ብቻ ሳይሆን በተግባራዊነቱም ነው።

የነፃ ገበያንና የሊበራሊዝምን ጉዳይ በሚመለከት አሜሪካንና የተቀሩት የምዕራብ አገሮች ሊያስተምሩን እንደሚፈልጉት እነሱ እንደፈለጉ ገብተው የሚጨፍሩባትን አገር እን ድናመቻችላቸው እንጂ ያማረችና የበለጸገች ኢትዮጵያን እንድንገነባ ፣ እንዲሁም ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድንከበር አይደለም። ድህነትን ፈልፋይ ፖሊሲያቸውን ተግባራዊ እያደረግን አቅመቢስነታችንን ለዘንተ-ዓለም ለማቆየት እንጂ። እስካሁን በታሪክ እን ደታየውም በአይ ኤም ኤፍና በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚክ ፖሊሲዎች አንድም አገር የበለጸገ የለም። ከውጭ የሚመጣው ዕርዳታ ወይም ብድር የባሰ ደሀ እያደረገን እንደሚመጣ ያለፈው አስራ አራት ዓመት በሚገባ አረጋግጧል። በ$ 21 በሊዮን የባሰ ድህነትን ከማትረፍ በስተቀር አልበለጸግንም። እንደዚህ ዐይነቱም ዕርዳታ የሰውን የተፈጥሮ የማሰብና የመስራት ኃይል የሚጻረር ፣ ማንኛውም ሰው እጅና እግር እስካለው ድረስ መስራትና ሀብት ማትረፍ ይችላል ፣ ኑሮውንም ማሸነፍ ይችላል የሚለውን ተፈጥሮአዊ ህግ የሚፃረር ነው። ተመጽዋች ምንጊዜም ተመጽዋች ሆኖ ነው የሚቀረው። ስለዚህም የአገራችን ችግር የነፃ ገበያ ጉዳይ ሳይሆን ስርዓት ያለው ሀብትን የሚያዳብር የሰራ ባህል አለመኖር መሆኑን ተረድተን በአዲስ መንፈስ መነሳት ያለብን ይመስለኛል። ከዚህ ስንነሳ ከዛሬው አገዛዝ ከስልጣኑ መባረር ባሻገር የምናስተጋባቸው መፈክሮች ፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ለሁሉም ህብረተሰብ የሚያገለግል የኢኮኖሚ ግንባታ ፣ ዲሞክራሲያዊ ነፃነትና እኩልነት ፣ በማንም የውጭ ኃይል ሊደፈር የማይችል ብሄራዊ ነፃነት የትግላችን አርማ መሆን አለባቸው። እነዚህን ከርዕዮተ ዓለም ውጭ የሆኑ መፈክሮችንና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ሊያካትቱ የሚችሉ መርሆችን እንደ መሰረታዊ ሀሳቦች/ፕርንሲፕልስ/ ይዘን ስንታገል ብቻ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ብሩህ መንገድ ልንጠርግላቸው እንችላለን። የተቃራኒውን ማድረግ ወይም ደግሞ በውጭ ኃይል ተማምነን አገራችንን እንገነባለን ማለትና ነፃነትን እንቀዳጃለን ማለት ዘበት ብቻ ሳይሆን የስልጣኔውንም ዘመን እንዲራዘም ማድረግ ይሆናል።

ፈቃዱ በቀለ /ከበርሊን

**<u>መነበብ ያለበት መጽሀፍ</u>**

**John Perkins, Confessions of an Economic Hit Man; San Franciscon, 2004**

EthioLion.Com